**DSpace Institution**

| **DSpace Repository** | **http://dspace.org** |
| --- | --- |
| Ethiopian Languages and Literature - Amharic | Thesis and Dissertations |

2018-11-05

# þÿ - è ;M - • 5p *ë e v}(Guide þÿWriting strategies ) è ;M } s• þÿp•3=•u• è `u “-`11› -M pp³

þÿ¥ ’, 0K

http://hdl.handle.net/123456789/9106

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

# ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

መምህራን መር የመጻፍ ክሂልን ሲያስተምሩ ልማዳዊ የሆነ የማስተማር ብልሀትን በማስወገድ ከተማሪዎች ፍላጎትና ተነሳሽነት አንፃር መፃፍን እንዲለማመዱ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ተለምዷዊ የሆኑ የማስተማር ብልሀቶች ተማሪዎች ራሳቸዉን ችለው እንዲፅፉ የሚያደርጉ ስለሆኑ ስህተታቸውን እንዳይረዱ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ብልሀት ተማሪዎች ከመምህሩ የሚጠብቁት ነጥብ(ዉጤት)ብቻ ነው (አንዋርቲኒ 2012)፡፡ መር መፃፍን የማስተማር ብልሀት ተማሪዎች ባላቸው የመጻፍ ችሎታና ፍላጎት እንዲሁም ዝንባሌ ተመድበው መፃፍን የሚማሩበት ብልሀት ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎችን በመፃፍ ብቃታቸው ዉጤታማና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡ የዚህ ብልሀት ዋናው ገፅታ ተማሪዎች በመምህራቸው እየተመሩ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው የመፃፍ እድገታቸውን እየቃኙና እየገመገሙ ማስተማር ነው፡፡ ይህ የማስተማር ብልሀት የተማሪዎችን የመፃፍ ችግር ቀስ በቀስ ይቀንሳል፡፡ ምክንያቱም መምህሩ በነጠላም ሆነ በቡድን ድጋፍ በማድረግና በመጻፍ ትምህርት ጊዜ በጋራ እንዲነጋገሩ ስለሚያደርግ ነው፡፡ ከመጻፍ ክሂል ትምህርት በኋላም ስለስራቸው በመወያየት ችግሮቻቸውን እንዲያስወግዱ ዕድል ይሰጣል( ባችቲያርና ሳጋላ 2012)፡፡

የቀድሞ የመጻፍ ትምህርት ንድፈሀሳብ፣አእምሮታዊ ሞዴል(cognitive models)በመጻፍ ትምህርት ዉስጥ ተነሳሽነትን እንደዋና ጉዳይ ትኩረት አይሰጠዉም ነበር፡፡ እንዳዉም እንደ አንድ የመጻፍ ትምህርትን የመፈለግ ምልክት ተደርጎ ይቆጠር ነበር( ሀይስና ፍላወር 1980 )፡፡ ነገር ግን ብሬይተና መስካርዳማሊያ(2007) ተነሳሽነት በራሱ የሚጠቀስ ሞዴል የለዉም ከሚለው ሀሳብ በመነሳት ከመጻፍ ትምህርት ጋር አያይዘው ማጥናት ጀመሩ፡፡ ከዚያም ሀይስ (1996) በአዲስ መንፈስ ተነሳሽነትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አያይዘው አጥንተዋል፡፡ የጥናቱ ዉጤትም የሚያመለክተው ተነሳሽነት የመጻፍ ትምህርት ግብ እንዲመታ ቁልፍ ተግባር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

መር መፃፍን የማስተማር ብልሀት በተለይ ለጀማሪ ጸሀፍት በቃላት፣ በአረፍተነገሮችና በረጃጅም ፅሁፎች መካከል ያለዉን ዝምድና እንዲረዱ ያስችላቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ተማሪዎች

የመጻፍ ሂደትን በቅደም ተከተል በአእምሮቸው እንዲቀርጹ በማድረግ ወጥ ፅሁፍ እንዲፅፉ ይረዳቸዋል (የህፃናት ትምህርት ክፍል ትምህርት ቤትና ቤተሰብ 2007) ።

ሚሊይ (2009) እንደገለፁት መር መፃፍን የማስተማር ብልሀት ስኬታማ እንዲሆን አጫጭር ታሪኮችን በመንገር ማስተማር ጠቃሚ ነው። አጫጭር ታሪኮችን ለተማሪዎች መንገር አእምሯቸውን ብሩህ በማድረግ የመፃፍ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የጎላ አስተዋፅኦ አለው።

በተጨማሪም ዞልታ (2001) እንዳብራሩት የተማሪዎች ዉጤታማነት የሚወሰነው በተደጋጋሚ በሚያደርጉት ልምምድና ቁርጠኛ በሆነ ተነሳሻነት ነው። ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ደግሞ ክፍል ዉስጥ የጎላ ተሳትፎ ሲኖራቸው ተነሳሽነት የሌላቸው ተማሪዎች ግን የተማሩትን እንኳን ለመመለስ ይቸገራሉ። በአጠቃላይ ከፍተኛ የሆነ ተነሳሽነት ለከፍተኛ መሳካት መነሻ እንደሆነ ሀንዲያኒ ፣ናዩማንና ማዲ(2013) ገልፀዋል። ሀርመር (2004)ን በመጥቀስ አላንገር (2015) እንደገለፁት በመር መፃፍ ሂደት ዉስጥ የመጨረሻው ረቂቅ እስከሚፃፍበት ድረስ አራት ደረጃዎች አሉት። (1) የማቀድ ደረጃ ሲሆን ተማሪዎች ምን መፃፍ እንዳለባቸው የሚወስኑበት፣ መረጃዎችንና ሀሳቦችን በአእምሮቸው የሚያደራጁበት ደረጃ ነው። በማቀድ ደረጃ ጊዜ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች የሚጽፉበትን አላማ መወሰንና እዉነታን መሰረት ባደረገ ቅደም ተከተል ይዘቱን ማስቀመጥ ነው። (2) ንድፍ የመፃፍ ደረጃ፣ ይህ ደረጃ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በወረቀት ላይ ለማስፈር ሙከራ የሚያደርጉበት ነው። በተጨማሪም ርዕሳቸውን መሰረት በማድረግ ስህተትን ሳይፈሩ ጊዜያዊ የሆነ ሀሳባቸውን የሚፅፉበት ደረጃ ነው። (3) የእርማት ደረጃ፣ ይህ ደረጃ የፅሁፍ ንድፋቸውን ከአላማቸው አኳያ ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን እንዲሁም ያስፈሩት ሀሳብ ግልፅነት የጎደለውና አሻሚነት ያለው እንዳይሆን ለማረጋገጥ ደጋግመው የሚያነቡበት ነው። የፅሁፉን እርማት አቻ ተማሪዎች ወይም መምህሩ በቃል ወይም በፅሁፍ ሊሰጡት ይችላሉ። ይህም ተማሪዎች የፃፉትን እንዲከልሱና እንደገና አስተካክለው እንዲፅፉ ዕድል ይፈጥርላቸዋል (4) የመጨረሻውን ረቂቅ መፃፍ፣ ይህ ከእርማት በኋላ የሚፃፍ ዋናው ፅሁፍ ሲሆን መጀመሪያ ከተፃፈው የንድፍ ፅሁፍ ይለያል ።ይኸውም በእርማት ጊዜ የተሰጡት ማስተካኪያዎች ተካተው ያለቀለት ፅሁፍ የሚዘጋጅበት ደረጃ ነው። እነዚህ አራት ደረጃዎች በአንድ የመጻፍ ትምህርት ዉስጥ ተለያይተው የሚገኙ ሳይሆኑ አንድ ላይ በቅደም ተከተል የሚከናወኑ ናቸው። ምክንያቱም ሁሉም በመፃፍ ሂደት የሚተገበሩ የመፃፍ አላባዎች ስለሆኑ ነው።

እንደኦካስኩዝ (2007) አገላለፅ ደግሞ መር መፃፍን የማስተማር ብልሀት ተማሪዎች በሞዴልነት ተደልድለው፣ ስራቸውም በፅሁፍ ሂደት ተቃኝቶ የሚበረታታበትና ራሳቸውን የሚያጎለብቱበት ሂደት ነው፡፡ መምህሩ ለክፍሉ ተማሪዎች ሁሉ የማስተማር ብልሀቱን ተግባራዊ እያደረገ፣ ተማሪዎችን እያበረታታ የተማሪዎችን ልምምድ በመገምገም ከየቡድኑ ፈቃደኛ የሆኑ ተማሪዎች የፅሁፍ ስራቸውን እንዲያነቡ በማድረግ ጣልቃ ገብቶ ስህተታቸውን ለማረም ያስችለዋል፡፡ የመምህሩ ባህሪይ ተስማሚነትና ከተማሪዎች ጋር ያለው መልካም ግንኙነት፣ የማስተማር ብልሀቱን ጥሩ መሆን፣ የክፍሉ የመማር ማስተማር ድባብ ደስተኛነት በተጨማሪም ለተማሪዎች ምቹ የሆነ የተማሪዎች አደረጃጀት መኖር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታንና ተነሳሽነት እንደሚያሳድግ ዞልታ (2001) ገልጸዋል፡፡

ማርሄኒ (2005) በበኩላቸው እንደገለጹት ተነሳሽነት ማንኛዉንም ተግባር ደረጃውን ጠብቆ ለማከናወን መሰረት ነው፡፡ ትሮያጋሪ (2001) ደግሞ  የመፃፍ ክሂል ችሎታንና ተነሳሽነትን ከተማሪዎች ባህሪይ ጋር አያይዘው ሲገልፁ ተማረዎች በመፃፍ ክሂል ትምህርት ጊዜ የማይሳካላቸው ከሆነ ለመፃፍ ተነሳሽነት አይኖራቸውም፡፡ ምክንያቱም በራስ የመተማመን ችግር ስለሚገጥማቸው ነው፡፡ ስለሆነም ተማሪዎችን በመደገፍ ጥሩ አድርገው እንዲፅፉ ማበረታታት ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም ባንዱራ(1986)፣ለንዛና ሶበሪን (1987)፣ ፖሪስና ዊናግሬድ(1990) ና ዊንግ (1994) እንዳብራሩት ተማሪዎች ለራሳቸው የሚሰጡትን ግምት አሉታዊ ከሆነ በመፃፍ ክሂል ዉጤታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች ሂደት ተኮር ብልሀትን የሚማሩ ከሆነ የሚሰጣቸውን ግብረመልስ መነሻ አድርገው የመፃፍ ክሂላቸውን ያጎለብታሉ::

ሌላው የተነሳሽነት ችግር የሚያጋጥመው ራስን በመቆጣጠር የመፃፍ ልምድ ማነስ ነው፡፡ ይህን ልምድ መረዳት ከተቻለ ራስን በማበረታታት የመፃፍ ልምድ ሊስተካከል ይችላል ፡፡ ግርሀምና ሀሪስ (1994) እንደገለፁት ከጥገኝነት ነፃ የሆነ ተነሳሽነት፣ ለመፃፍ ክሂል ዉጤት ያለውን በጎ አስተዋፅኦ መተንበይ ይችላል፡፡

መር የመፃፍ ብልሀት መምህራንን በማሳተፍ ተማሪዎች አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ቡድኖች ሆነው የየግላቸውን ጽሁፍ ለመጻፍ የሚያደርጉትን ጥረት የሚያግዙበት፣ ለተማሪዎች ፅሁፍ ምላሽ የሚሰጡበትና በመጻፍ ሂደቱ የተማሪዎችን ሀሳብ የሚያሰፍሩበት የማስተማር ብልሀት ነው (ትራይለር 2010) ፡፡ ፋራስ (2008) እንደገለፁት ደግሞ መር የመፃፍ ክሂል ብልሀት ተማሪዎችን አነስተኛ ቁጥር በያዙ ቡድኖች በመመደብ በጋራ ፍላጎት ላይ የተመሰረተና

መምህሩ ከተማሪዎች ጋር ተቀራርቦ እገዛ የሚያደርግበት ብልሀት ነው። ይህም ተማሪዎች የመፃፍ ክሂልን ከየት ጀምረው ጥሩ ፀሀፊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይመራቸዋል።

ብሪንደሊንና ሽናደርን (2002)ን ጠቅሰው ላን (2011) እንዳስረዱት የመፃፍ ክሂል መር መፃፍን፣ ሞዴሊንግን፣ ተጋርቶ መጻፍንና በተራክቦ የመጻፍ ስልቶችንና ብልሀቶችን ማካተት አለበት ። በተጨማሪም የተማሪዎችን የመፃፍ ሂደትና ብቃት ለማሻሻል ስዕሎችን እንደመር መፃፍን ማስተማሪያ ብልሀት እንደሚጠቀሙም ገልፀዋል። ስዕሎችን እንደመር መፃፍን ማስተማሪያ ብልሀት መጠቀም ጀማሪ ፀሀፊዎችን በታላሚዉ ቋንቋ ሀሳባቸዉን በሚገልፁበት ጊዜ እንዳይጨነቁና የመፃፍ ተነሳሽነታቸውን እንዲያጎለብቱ ይረዳቸዋል።

የቅርብ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ደግሞ መር መፃፍን ማስተማሪያ ብልሀት የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታና ተነሳሽነት ለማሳደግ፣ የመፃፍ አካባቢን ለመፍጠር ይረዳል (ላን 2011)። እነዚህ መፃፍን የሚያበረታቱ የመማር አካባቢዎች ፅሁፎች፣ ስዕሎች፣ የሚደመጡና የሚታዩ ቪዲዮዎች ሲሆኑ የተማሪዎችን የመፃፍ ፍላጎትና ፈቃደኝነት የሚያነሳሱ እንደሆኑ ገልፀዋል። ዲያን(2009) ደግሞ የተማሪዎችን የመፃፍ ችግር ለመፍታት መር የመፃፍ ብልሀትን መጠቀም ጥሩ እንደሆነ ገልፀዋል። ምክንያቱም መር የመፃፍ ብልሀት መፃፍን ቀለል አድርገው እንዲያዩትና ለመፃፍ ልምምድ እንዲያደርጉ ስለሚረዳቸው ነው። በተጨማሪም መር መፃፍ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው በሚፅፉበት ወቅት አንድን ፅሁፍ አስፋፍተው እንዲፅፉ የሚረዳ ብልሀት እንደሆነ አስረድተዋል።

በተጨማሪም ብራዉን (2001) እንደገለፀው መር የመፃፍ ክሂልን ማስተማሪያ ብልሀት የመፃፍ ችሎታንና ተነሳሽነትን የሚያሳድግና ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ እንዲገልፁ የሚያበረታታ ነው። በዚህ የመፃፍ ደረጃ ተማሪዎች በሚኖራቸው ለዉጥ የመፃፍ ሂደቱን በራሳቸው የሚቆጣጠሩበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። መምህራን የተማሪዎችን ፍላጎትና ዝንባሌ መነሻ አድርገው ለተማሪዎቹ እገዛ ያደርጋሉ። በአጠቃላይ እነዚህ ደረጃዎች መፃፍን ለመማር እንደ አንድ ግብ ተደርገው ይወሰዳሉ። ተማሪዎች መምህራቸው ከሚሰጧቸው ሀሳብ በመነሳት በተናጠል የራሳቸውን ፅሁፍ ያዘጋጃሉ። ይህም ተማሪዎች ርስበራሳቸው እንዲሁም ከመምህራቸው እንዲማሩ ያበረታታል። የመፃፍ ክሂል በመር መፃፍ፣ በቁጥጥር መፃፍ፣ እና ራስን ችሎ መፃፍ የሚሉ ሶስት ደረጃዎች አሉት( ብሮዉተን 2003)።

ሽናሀን (2004) ን ጠቅሰው ኪስ (2000) እንዳብራሩት በመለስተኛና በሁለተኛ ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች የሚሰጣቸው የመፃፍ ተግባር በከፍተኛ ደረጃ ማሰብን የሚጠይቅና ዉስብስብ የሆነ

የመፃፍ ብልሀቶችን ተግባራዊ የሚያደርግ ነው። ለመማር ማስተማር ሂደት የተነደፈውን መርሀትምህርት ተግባራዊ ማድረግ ተማሪዎችን በመፃፍ ክሂል ላይ ያላቸውን ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ለማሳደግ እንደመሳሪያ ሆኖ ያገለግላል።

እንደኦንታርዮ (2005) ገለፃ መር ፅሁፍ የሚያተኩረው ፣ መምህሩ ከተማሪዎች ጋር በመሆን ቀድሞ የነበራቸውን ዳራዊ እዉቀት በመጠቀም የሚተገብሩት የመጻፍ ሂደት ነው። መር መጻፍ ሲባል ተማሪዎች የመጻፍ ተግባራቸውን እንዴት እንደሚያካሂዱ፣ምን ለማለት እንደፈለጉና እንዴት መፃፍ እንዳለባቸው ፍንጭ የሚሰጥ የማስተማሪያ ብልሀት ነው። የመር መጻፍ ዋናው አላማ ለአንባቢያን ቁምነገርን ማስተላለፍና ተማሪዎችን ጥሩ ፀሀፊዎች እንዲሆኑ ማስቻል ነው ። ስለዚህ የመምህራን ተግባር ተማሪዎች የሚያዘጋጁትን ፅሁፍ በጋራ በመሆን ከፅሁፍ ሂደትና ዕድገት አኳያ በማጤን የመጻፍ ችሎታቸውና ተነሳሽነታቸውን ማዳበር ነው። መር የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ብልሀትን ለመተግበር የሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ተግባራዊ መደረግ አለባቸው (1) ሶስት ወይም አራት የአባላት ቁጥር ያለው ቡድን በማደራጀት ለመፃፍ ክሂል የሚሆኑ መረጃዎችን ይሰበስባሉ። ለምስሌ ከስዕል፣ ከቻርት፣ ከግራፍ፣ እንዲሁም ያዩትን ወይም የሰሙትን ሁነት በማስታወስ ፍንጭ የሚሰጡ መረጃዎችን ይሰበስባሉ(2) የሰበሰቡትን መረጃ መሰረት በማድረግ ስለሰዋሰው ስህተት፣ ስለቃላት አጠቃቀም፣ ስለ ዓረፍተነገር አወቃቀር ስለ ስርዓተነጥብ አጠቃቀም ሳይጨነቁ በየግላቸው የመጀመሪያውን ረቂቅ ይፅፋሉ። (3) የቡድን አባላት በየግላቸው የፃፉትን የመጀመሪያውን ረቂቅ በቡድን በመሆን ሀሳብ ይለዋወጡባቸዋል። ማን ምን ፃፈ ለምን እንዲህ ፃፈ፣ እንዴት ፃፈ በሚሉት ሀሳቦች ዙሪያ እያንዳንዱን ፅሁፍ ከመምህራቸው ጋር በመሆን ይተቻሉ። (4) መምህራንና ተማሪዎችን በጋራ በመሆን በተከሰቱት ጉድለቶች ላይ የአርትኦት ስራ ይሰራሉ። በመጨረሻም የየቡድኑ አባላት የተሰጣቸዉን አስተያየት ግምት ዉስጥ በማስገባት የመጨረሻዉን ፅሁፍ አስተካክለው ያቀርባሉ። መምህሩም ማጠቃለያ አስተያየት ሲሰጡ ተማሪዎች ማሻሻያ የሚሆን ሀሳብ ይወስዳሉ።

ከዚህ በተጨማሪም ጊብሶን (2008) እንዳብራሩት መር የማስተማሪያ ብልሀት አነስተኛ የአባላት ቁጥር ያላቸው ቡድኖችን በማደራጀት ለሀያ ደቂቃ ያህል የሚሰጥ፣ ተነሳሽነትን የሚፈጥርና የመጻፍ ችሎታን የሚያሳድግ መፃፍን ማስተማሪያ ብልሀት ነው። እነዚህ በአነስተኛ ቁጥር የተዋቀሩ ቡድኖች በየተግባራቱ ተለዋዋጭ ይሆናሉ።እንደየአመለካከታቸውና እንደየፍላጎታቸው በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ ቡድኖችን ይመሰርታሉ። ይህንን የማስተማር ብልሀት ዉጤታማ የሚያደርገው ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በአንድ ላይ ሲሰባሰቡ ነው።

ጊብሶን(2008) መር የማስተማር ብልሀት አተገባበር እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡ በቅድሚያ ተማሪዎች የአነበቡትን ወይም የተመለከቱትን አስገራሚ ወይም አሳዛኝ ታሪክ ለቡድን አባላቱ ይገልፃሉ፡፡ በታሪኩ ዙሪያ ሃሳባቸውን በንግግር ሲገልፁ የስነልሳን ችሎታቸውም ይለካል፡፡ በመቀጠልም በቡድን አባላቱ የተገለፁትን ታሪኮች አንዱን በመምረጥ በየግላቸው ሀሳብ አደራጅተው እንዲፅፉ ይደረጋል፡፡ በሚፅፉት ሀሳብ ዉስጥ የአረፍተነገር አወቃቀር፣ ፊደሎችንና ስርዓተነጥቦችን በአግባቡ እንዲጠቀሙ መምህሩ ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም መር መፃፍን የማስተማሪያ ብልሀትንና የእለቱን የመፃፍ ትምህርት እንዴት እንደሚያዋህዱ ከተማሪዎች ጋር በግልፅ መወያየት ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም በቡድን ሆነው የተወያዩትን ሀሳብ በየግላቸው እንዲፅፉ ከአምስት እስከአስር ደቂቃ በመስጠት እንዲጽፉ ይደረጋል፡፡ የሚፅፉትን ፅሁፍ ግን አጭርና የተሟላ መሆን አለበት፡፡ በሚፅፉበት ጊዜ መምህሩ መቆጣጣርና ማገዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመጨረሻም የጻፉትን ፅሁፍ ለአንባቢ ማስደመጥ በቀጣይ ለሚፅፉት ፅሁፍ መነሻ ይሆናቸዋል፡፡

እ.አ.አ ከ1960 ዓ.ም በፊት የመፃፍ ክሂል ትኩረት የሚያደርገው በስዋስው፣ በፊደላት፣ በ ስርዓተነጥቦችና በእጅ ፅሁፍ ላይ ነበር፡፡ ዘዴዉም ትኩረት ያደርግ የነበረው በአረፍተነገር አመሰራረት ላይ እንጅ በድርሰት መፃፍ ላይ አልነበረም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመፃፍ ክሂል በይዘት ዕዉቀት ላይ ያተኩር እንደነበር ሃዉኪንስና ሪዛሊ(2012) አስረድተዋል፡፡ የመፃፍ ክሂል ሂደታዊ የሆነ ቅድመ መፃፍ እስከመጨረሻው ረቂቅ ድረስ ተከታታይ የእድገት ደረጃዎች ያሉት ነው ያሉት ደግሞ ሙራይ(1969) ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ኢሚግ (1971) ን በመጥቀስ አላንጋር (2015) እንደገለፁት የመፃፍ ሂደት በቀላሉ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የሚሸጋገር ሳይሆን በተደጋጋሚ የሚከናወንና የሚፈተሽ ተግባር ነው፡፡ ይህ አይነቱ ሂደትተኮር እንደሆነ አልተንና ትሮምብላ (2001) ገልጸዋል፡፡

ፍሉድ (2000) ን በመጥቀስ ጊብሰን (2008) እንደገለፁት የቡድን ስራን ማዘዉተር የመፃፍ ችሎታ እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ከሌሎች ጋር ጥገኛ በመሆን የመፃፍ ተነሳሽነታቸውን ያሳጣቸዋል፡፡ ነገር ግን በመር የመፃፍ ትምህርት ጊዜ የመምህሩ ክትትል ስላለበት ለዚህ አይነቱ ችግር አይጋለጡም፡፡ በመር ማስተማር ጊዜ ዋናዉ ጉዳይ ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ የመፃፍ ተግባርን ሲማሩ ብዙ እንዲፅፉ ሳይሆን በመፃፍ ክሂል ዉስጥ ያሉትን ትንንሽ ጉዳዮች ተረድተው አጭርና ያለቀ ፅሁፍ እንዲያዘጋጁ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም መር የመጻፍ ክሂልን ማስተማሪያ ብልሀቶች የመጻፍ ችሎታንና ተነሳሽነትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና መመርመር ይሆናል፡፡

## 1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር

በናይጀሪያ ካዱና ከተማ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች በ2011 የነበሩ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብና የመጻፍ ክሂል ደረጃቸው በ4ኛና 5ኛ ክፍል ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ሚላር (2014) አስረድተዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ችሎታ እድገት የሚያደናቅፉ ነገሮች በርካታ ቢሆኑም ዋናው ምክንያት ግን የራሳቸው የተማሪዎቹ የመጻፍ ልምድ አለመኖር እንደሆነ ጆሴፍ (2013) ያስረዳሉ፡፡ ይሁንና በመማር ማስተማሩ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን የተለያየ ዘዴ በመጠቀም መቅረፍ እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ በመር ብልሀት መጻፍን በሚማሩበት ጊዜ የመጻፍ ችሎታቸውንና የራስ ተነሳሽነታቸውን እንዴት ማሳደግ እንደሚችሉ በዚህ ጥናት ይፈተሻል፡፡

ሌላው ተማሪዎች መጻፍን በክፍል ዉስጥ ከሚማሩት በተጨማሪ በእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸው ዉስጥ መጻፍን ለመለማመድ ምንም ጥረት ሲያደርጉ አይታዩም፡፡ በዚህም ምክንያት ሀሳባቸውን በጽሁፍ ለመግለጽ የሰዋስው፣ የቃላት፣ የስርአተነጥቦችና የአረፍተነገር አወቃቀር ችግር እንደሚገጥማቸው ጆሴፍ (2013) ገልጸዋል፡፡

ብራውተን (2003) እንዳብራሩት ደግሞ ተማሪዎች መጻፍን በሚለማመዱበት ጊዜ ብዙ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ነጥቦች አሉ፡፡ ይሁንና ተማሪዎች በሚጽፉበት ወቅት እነዚህን ትኩረት የሚሹ ነጥቦች ከግምት ዉስጥ እንደማያስገቡ አብራርተዋል፡፡ ለምሳሌ በተማሪዎች ጽሁፍ ዉስጥ የቃላት አጠቃቀም ችግር፣ ሰዋስዉን በትክክል የመጠቀም ችግር፣ መጻፍ የተፈለገው ይዘትና የአጻጻፍ ስልት ያለማዛመድ ችግርና መጻፍ የፈለጉትን ሀሳብ በብቃት መግለጽና የማሳደግ ችግር በብዛት የሚታዩ ችግሮች ናቸው፡፡ እነዚህ በሆጤ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታና ተነሳሽነት ዝቅተኛ በመሆኑ የመጻፍ ክሂል ፈተና ውጤታቸውም ከደረጃ በታች መሆኑን አጥኝዋ መጻፍን በምታስተምርበት ጊዜ ያጋጠማት ችግር ነው፡፡ የመጻፍ ክሂል መልመጃዎች አተገባበር ከሌሎች መልመጃዎች አተገባበር አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑና የመጻፍ ክሂል ትምህርትን ሲማሩ የመጻፍ ተነሳሽነት አለመኖራቸው ለዚህ ጥናት መነሻ ምክንያት ሆኗል፡፡

ታችባ (2008) እንዳስረዱት እ.አ.አ በ2007 ዓ.ም አንድ ሶስተኛ የሚሆኑ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችንና አንድ አራተኛ የሚሆኑ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ፈተና ተፈትነው ዉጤታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለዚህ ችግር እንደ ምክንያት የተጠቀሰው ደግሞ ተስማሚ ያልሆነ የማስተማር ብልሀት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ብሬድካምፕ

(1987) በበኩላቸው የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ደረጃ በጣም የወረደ መሆኑን አስረድተዋል።

መር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ችሎታን በማሳደግ ረገድ ያለውን ሚና የሚፈትሹ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል። የተወሰኑት ጥናቶቹ ዉጤትም እንደሚያሳየው በመር ማስተማሪያ ብልሀት መጻፍን ማሰተማር የተማሪዎችን ዉጤት ማሳደግ ብቻ ሳይሆን የመጻፍ ፍላጎታቸውንና ተነሳሽነታቸውንም ጭምር እንደሚያጎለብት አረጋግጠዋል።

መር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀት በመጻፍ ችሎታና በመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ያለውን ሚና የሚፈትሹ ጥናቶች ሁሉም በዉጭ ሀገር የተሰሩ ናቸው። ጆሴፍ (2013) በኢንዶኔዢያ፣ ሀንዲያኒ እና ሌሎች (2013)፣ አህማዱ ቤሎ ዩኒቨርሲቲ (2013) በቋንቋት ትምህርት ክፍል የተጠና ጥናት፣ሉህ (2014)፣ማካርተር(2002)፣ሁንግ (2012) በቻይና ፎርሞሳ ዩኒቨርሲቲ የተጠኑ ናቸው። እነዚህ ጥናቶች መር መጻፍን ማሰተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ክሂልን ከማሳደግ አኳያ ያለውን ሚና የፈተሹ ጥናቶች ናቸው። ከፊሎቹ ደግሞ ተነሳሽነትን ከመጻፍ ክሂል ችሎታ ጋር አያይዘው የፈተሹ ናቸው።

የጥናቶቹ ትኩረት መር የማስተማር ብልሀት በመጻፍ ክሂል ችሎታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ የሚፈትሹ ቢሆኑም የተወሰነ ልዩነት ይታይባቸዋል። ጆሴፍ (2013) መር የማስተማር ብልሀት ገላጭ ድርሰትንና አጫጭር ዜናዎችን ለመጻፍ የጎላ አስተዋጽኦ እንዳለው ሲገልጽ የመጻፍ ተነሳሽነትን ከማጎልበት አንጻር ያለውን ሚና ለመፈተሽ አልሞከረም።

ሁንግ (2012) በቻይና በሚገኝ ፎረሞሳ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋ ትምህርት ክፍል የተጠና ጥናት በስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት የተከናወነ ነው። 66 ተጠኝዎችን ቅድመፈተና ከተፈተኑ በኋላ ለሁለት ቡድን በመክፈል 33 ተማሪዎችን የቁጥጥር ቡድን፣33 ተማሪዎች ደግሞ የሙከራ ቡድን በማድረግ ጥናቱ ተካሂዷል። የተማሪዎች አማካይ እድሜ 12 አመት ነው።

ለሙከራ ቡድኑ ለ12 ሳምንታት ተከታታይ ስልጠና ተሰጥቷል። በመጨረሻም ድህረፈተና በመስጠት በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድን መካከል የለው ልዩነት በነጻ ናሙና ልይይት (one-way anova) ተተንትኖ የተገኘው የጥናት ዉጤት፣መር ማስተማሪያ ብልሀት የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ፣የመጻፍ ተነሳሽነትና በተዝናኖት መጻፍ ጋር አዎንታዊ ግንኙነት እንዳለው በዚህ ጥናት ተረጋግጧል። ይህ ጥናት ሀንዲያኒ ና ሌሎች (2013) ፣ጆሴፍ (2013)፣

ማካርተር (2002)ና ሉህ (2014)፣ጋር የሚለየው በተዝናኖት መጻፍን እንደ አንድ ተላዉጦ ማጥናቱ ነው፡፡

ሀንዲያኒ እና ሌሎች (2013) መር የመጻፍ ብልሀትን ከተማሪዎች የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነት ጋር አጣምረው አጥንተዋል፡፡ ይህ ጥናት መር የመጻፍ ብልሀትን ከመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነት ጋር አያይዞ የሚፈትሽ ሲሆን የጆሴፍ (2013) ጥናት ደግሞ መር የማስተማር ብልሀት ከተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ማነስ፣ ከመምህሩ የማስተማር ብልሀት ችግር፣ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችና ከተማሪዎች የእርስ በእርስ ተራክቦ አለመኖር ጋር ተያይዞ የቀረበ ነው፡፡ ስለዚህ ጥናቱ ተነሳሽነትን እንደአንድ ተላዉጦ ሳይሆን ለማየት የሞከረው የመጻፍ ክሂል ችሎታን የሚያደናቅፉ ጉደዮች በሚል መሆኑ ከሀንዲያኒና ሌሎች(2013) ጥናት የተለየ ሆኗል፡፡

ሀንዲያኒና ሌሎች (2013) በኢንዶኔዥያ የተጠናው ጥናት የተካሄደው በ134 የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን ተማሪዎቹ ከየክፍሉ በእድል ሰጭ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ተመርጠው በጥናቱ ተካተዋል፡፡ እነዚህን ተማሪዎች ለአራት ክፍል በመክፈል ሁለቱን ቡድን ተማሪዎች መር መጻፍን የማስተማር ብልሀትን በመጠቀም የተማሩ ሲሆን ሌሎቹን ሁለት ክፍል ተማሪዎች ግን የቁጥጥር ቡድን በማድረግ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ በመር መጻፍ የማስተማር ብልሀት የተማሩት ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታቸውና የመጻፍ ተነሳሽነታቸው ከፍተኛ እንደሆነ የጥናቱ ዉጤት አረጋግጧል፡፡

ይህ ከማካርተር (2002) ፣ ሁንግ (2012) ና በናይጀሪያ አህማዱ ቤሎ ዩኒቨርሲቲ የጥናት ግኝት ጋር የሚያመሳስለው ጭንቀት በመጻፍ ችሎታና በመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ያለውን ተጽዕኖ በመፈተሽ ነው፡፡

ጆሴፍ (2013) በበኩላቸው "መር የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ብልሃት የመጻፍ ክሂልን በማሳደግ ረገድ ያለው ሚና" በሚል በስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሲሆን 61 ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል፡፡ ተማሪዎችን በሁለት ቡድን በመክፈል 30 ዎቹን ተማሪዎች የቁጥጥር ቡድን፣ 31ን ተማሪዎች ደግሞ የሙከራ ቡድን በማድረግ ምርምሩ ተከናዉኗል፡፡ በጥናቱ ሂደት ለምርምር ቡድኖቹ ቅድመመጻፍና ድህረመጻፍ ፈተና ተሰጥቷል፡፡ በመጨረሻም በመር መጻፍ የማስተማር ብልሀት የመጻፍ ክሂልን የተማሩ ተማሪዎች ገላጭ ድርሰትና አጫጭር ዜናዎችን በመጻፍ ችሎታቸው ከፍ ያሉ መሆናቸውን በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡ ከሁንግ (2012)ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የሁለቱም በከፊል ፍትነታዊ ስልት የተሰራ ሲሆን፣ ተነሳሽነትን  እንደ አንድ ተላዉጦ አለመዳሰሱ ደግሞ ልዩነታቸው ነው፡፡

ጆሴፍ (2013) ፣ ማካርተር (2002) ና ሁንግ (2012) እነዚህ ጥናቶች መር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ክሂል ችሎታን ከማጎልበት አንጻር የሚፈትሹ ናቸው፡፡ተነሳሽነት ያለመኖር የመጻፍ ችሎታን የሚያደናቅፍ መሆኑን በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡የሀንዲያኒና

ሌሎች (2013) ና የሉሀ (2014) ጥናት ዉጤት ደግሞ የሚያመለክተው የመጻፍ ክሂል ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ተነጣጥለው የማይታሰቡ ጉዳዮች መሆናቸውን ነው፡፡ በእነዚህ የጥናት ግኝቶች መካከል ያለውን ልዩነት መፈተሽ ለዚህ ጥናት የመጠናት ምክንያት ሆኗል፡፡

ይህ ጥናት በደሴ ከተማ አስተዳደር በሆጤ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሠናዶ ትምህርት ቤት መር መጻፍ የማስተማሪያ ብልሀት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታና ተነሳሽነትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለመፈተሽ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ያተኮረ ጥናት ስለሆነ በዋናነት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

1. መር የማስተማር ብልሀት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ያሳድጋልን?

2. መር የማስተማር ብልሃት የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ያሣድጋል ወይ?

## 1.3.የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች መር የመጻፍ ክሂልን የማስተማር ብልሃት የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታንና ተነሳሽነትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና መፈተሽ ሲሆን ጥናቱም የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡

1. መር የማስተማር ብልሃት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ማሳደጉን ለመፈተሽ
2. መር የማስተማር ብልሃት የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ማሳደጉን ለመመርመር

## 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

መር የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ክሂል ችሎታንና ተነሳሽነትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ማጥናት፣መር የመጻፍ ብልሀት ለመጻፍ ክሂል ይበልጥ ጠቃሚ እንደሆነ ከማሳወቅ ባሻገር ይህንን ብልሀት ተማሪዎች በመጠቀም የመጻፍ ሂደት ላይ የሚያጋጥማቸውን ችግር በመቅረፍ ጠቃሚነት አለው፡፡ ይህም ጥናት ቀጥሎ ያሉትን ጠቀሜታዎች በማስገኘት ረገድ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡

1. የመጻፍ ክሂል አስቸጋሪና ዉስብስብነት ያለው በመሆኑ ክሂሉን ለማጎልበት በሂደት ብዙ መስራትና ተደጋጋሚ ልምምድ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ግንዛቤ ለማስጨበጥ ያግዛል፡ ፡
2. ለቋንቋ መምህራን የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂልና የመጻፍ ተነሳሽነትን ለማሳደግ በመር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀት በመጠቀም የመጻፍ ክሂል ትምህርት እንዲያስተምሩ ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡
3. ተማሪዎች በመር የማስተማር ብልሀት ተምረው የተለያዩ የመጻፍ ክንዋኔዎችን በመስራት የመጻፍ ችሎታቸውንና የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን የማጎልበት አቅም እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል፡፡
4. በመጨረሻም ወደፊት ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያለው ጥናት ለሚያጠኑ ተመራማሪዎች የመነሻ ሀሳብ ለመስጠት ይጠቅማል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በደሴ ከተማ ፣ በሆጤ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚገኙ የ2010 ዓ.ም የ11ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በሚከታተሉ ተማሪዎች ላይ የተደረገ ሲሆን፣ የጥናቱ ትኩረትም መር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀት የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና መፈተሽ ነዉ፡፡

በከተማዉ አስተዳደር ሶስት የመንግስት መሰናዶ ትምህርትቤቶች ቢኖሩም በአመቺ ናሙና ዘዴ ሆጤ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርትቤት ተመርጧል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት አጥኚዋ በመደበኛነት የምትሰራበት ትምህርት ቤት በመሆኑ ጥናቱን በጥልቀትና በጥንቃቄ ለመስራት ስለሚያስችላት ነው ፡፡

በዚህ ጥናት ፒንካስ (1982) ና ራሚስ (1983) ያሻሻሉት መር መጻፍን ማስተማሪያ ሞዴል የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ለጥናቱ ተሳታፊነት የተመረጡ ተማሪዎችን ለማስተማር አገልግሎት ላይ ዉሏል፡፡

ይህ ሞዴል የተመረጠበት ምክንያት ተማሪዎች አካባቢያቸውን በመቃኘትና የገጠሟቸውን መልካምም ሆነ መጥፎ አጋጣሚዎች ወይም የሰሟቸውን ታሪኮች ወደጽሁፍ በመቀየር የመጻፍ ክሂል ችሎታቸውንና የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን በማጎልበት ረገድ እገዛ ስለሚያደርግላቸው የጥናቱን አላማ ከግብ ያደርሳል በሚል ነው፡፡

## 1.6 የጥናቱ ዉስንነት

መር የመጻፍ ክሂል  ማስተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ተነሳሽነትን ከማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለማሳየት ከተጠኑ ጥናቶች መካከል አጥኝዋ ያገኘቻቸው በአገር ዉስጥ የተጠኑ ጥናቶች ባለመኖራቸው የአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታን መነሻ ባለማድረጉ ዉስንነት ሊታይበት ችሏል፡፡

## 1.7 የቁልፍ ቃላት ብያኔ

1.መር መፃፍን ማስተማሪያ ብልሀት፡- በዚህ ጥናት መነሻ ሀሳብ በመዉሰድ ወይም ገጠመኞችን መነሻ በማድረግ ፣በቡድን በመሆንና በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በመወያየት የጋራ የሆነ ሀሳብ ከተወሰደ በኋላ ርዕሰ ጉዳዩን በየግል የሀሳብ ፍሰትን፣የስርአተነጥብ አጠቃቀምንና ተገቢነት ያላቸው አያያዦችን በመጠቀም በመምህሩና በአቻዎቻቸው እየተመሩ (እየታገዙ) ሀሳብን አብራርቶ በጽሁፍ ማስፈር የሚያስችል ብልሀት ነው፡፡

2. የመጻፍ ተነሳሽነት፡- በዚህ ጥናት ሀሳብን፣ስሜትን፣እንዲሁም በዙሪያ የሚታዩና የሚደመጡ ነገሮችን፣ ሀሳብ ደራጅቶ በወረቀት ላይ የማስፈር ችሎታን የማጎልበት ፍላጎት መኖር ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡-ተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

## 2.1. የመር መፃፍ፣የመጻፍ ችሎታና የመፃፍ ተነሳሽነት ትስስር

በመፃፍ ክህሎት ስነትምህርትና የመማር ብልሀት ዝንባሌዎች ላይ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል፡ ፡ ከነዚህም የጥናት ዘርፎች መካከል በሞዴል መፃፍ፣ በጋራ መፃፍ፣መር መፃፍ፣ ተዛምዶዊ መፃፍ በማሳያነት ቀርበዋል መር መፃፍ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ችሎታ እንዲዳብር፣ ሂደትን ተከትለው የመፃፍ ብቃት እንዲኖራቸዉና የመፃፍ ተነሳሽነት ኖሯቸው ለመፃፍ ከፍተኛ ጉጉት እንዲያድርባቸዉ የሚያደርግ የማስተማር ብልሀት መሆኑን አብራርተዋል፡፡ (ፒነልና ፋዉንታስ 1998)፣ (ሲ 1994)፡፡

ብሎግ(1988) በጥናታቸው እንደገለፁት መር መፃፍን የማስተማር ብልሀት የተማሪዎችን አእምሯዊ መነሳሳት ስለሚፈጥር በሚጽፉት መልዕክት ላይና በሚጽፉት ፅሁፍ ክብደት ላይ አዎንታዊ የሆነ አስተዋፅኦ አለው፡፡ የመፃፍ ክሂሎት ከሌሎች ክሂሎች የበለጠ ዉስብስብ ፣ጊዜን የሚፈጅ፣ የቃላትን ስኬትና ሰዋሰዋዊ ህጎችን (በዖታ፣ በቁጥር፣ በጊዜያት) ጠብቆ የመፃፍና የሚፈለገውን መልዕክት ለመፃፍ የሆሄያት አጣጣልና የስርዓተነጥቦችን አጠቃቀም ጨምሮ ንድፍ መንደፍ፣ ማስተካከልና ማረቅን የሚጠይቅ አድካሚ ክሂል ነው፡፡ ይህን ዉስብስብ የሆነ ተግባር ለማከናወን የተማሪዎች ተነሳሽነት መኖር ወሳኝ ነው፡፡ መር መፃፍ ደግሞ ተነሳሽነትን ለመፍጠር ተማሪዎች በጥሩ ቃላት፣ ጊዜያትንና ሰዋሰዋዊ ህግን ጠብቀው እንዲሁም ተገቢ የሆኑ ስርዓተ ነጥቦችን በመጠቀም የተቃና ፅሁፍ እንዲፅፉ ያግዛቸዋል፡፡

የመጻፍ ክሂሎት ችሎታንና የመጻፍ ተነሳሽነትን ለማዳበር መር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀት ተመራጭ ነው (ጋልብሬዝና ቶራንስ 2004፣64)፡፡ የመር መፃፍ አላማ ጀማሪ ፀሀፊዎች በመምህራቸውና በጓደኞቻቸው እየተመሩ (እየታገዙ) ከቃላት፣ ሀረጋትና አረፍተነገሮች አስካክ ጀምሮ ስህተታቸውን በማሰተካከልና በጭንቅላታቸው ዉስጥ መመዘኛ ነጥቦችን በማስረፅ፣ በመለማመድ ራሳቸውን ችለው የተስተካከለ ፅሁፍ እንዲፅፉ ማስቻል ነው (ሆልድችና ቹንግ 2003) ፡፡ የመር መፃፍ ልምምድን ኦክስኩዝ (2007) ሲገልፁ ተማሪዎች ችሎታቸውን ተጠቅመው የአቻ ምላሽንና የመምህሩን ፍትነታዊ እገዛ በማካተት እንዲፅፉ የሚያስችል ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡

ተማሪዎች ከመምህራቸውና ከአቻዎቻቸው ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያጠናክርና በመካከላቸው የመፈራራትን ስሜት የሚያስወግድ የማስተማሪያ ብልሀት በመሆኑ ተማሪዎች ክፍለ ጊዜውን

ወደውት፣ የመፃፍ ተነሳሽነት ኖሯቸው መፃፍን እንዲለማመዱ የሚያደርግ ብልሀት ነው፡፡ ሆልድና ቹንግ(2003) መር መፃፍንና የመጻፍ ተነሳሽነትን አጣምረው ሲገልፁት መምህሩ የትምህርት መርጃ ዘዴዎችን በማቅረብ ተማሪዎች በሙሉ ተነሳሽነት መፃፍን እንዲለማመዱ ማድረግ ነው፡፡ ቀድሞ የነበረዉን (ባህላዊው) መር መፃፍ ብልሃት መምህሩ በወረቀት በመፈተን፣ ሥዕልና የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን በማቅረብ እንዲለማመዱ ማድረግ ነበር አሁን ግን ተማሪዎች በቀረበላቸው ማዕቀፍ ዉስጥ ከአቻዎቻቸውና ከመምህሮቻቸው ጋር በመወያየትና በመተጋገዝ የራሳቸውንም የዉስጥ ችሎታ ጭምር በማዉጣት በነፃነት ስሜት የሚማሩበት አይነተኛ ብልሀት ነው፡፡

## 2.2. መር መጻፍ የመጻፍ ችሎታንና ተነሳሽነትን ለማሳደግ የሚከተላቸው ቅደም ተከተሎች

ግሬቭስ (1983) ን በመጥቀስ ጊብሰን (2008) እንዳብራሩት መር መፃፍን ማስተማር ብዙ ጊዜ የሚወስድና ወሰን ተዘጋጅቶለት የሚከናወን አይደለም፡፡ ነገር ግን ከበድ ያለ አገባብ ያላቸውን የመፃፍ ትምህርቶችን ተማሪዎች ወደውትና ተነሳሽነት ኖሯቸው እንዲማሩ መምህሩ ተማሪዎችን የሚደግፉበት ብልሀት ነው፡፡

ይህ የማስተማር ብልሀት አራት ዋና ዋና ደረጃዎች አሉት እነርሱም፡- ደረጃ (1) ይህ ደረጃ ተማሪዎች ልምዳቸውን በግልፅ የሚያሳዩበትና አዳዲስ መጻህፍትን አንብበው ትርጉሙንና ቋንቋውን እንዴት መረዳት እንዳለባቸው መምህሩ መመሪያ የሚሰጥበት ነው፡፡

ክላይ (1991፣265) እንደገለፁት መምህሩ፣ ተማሪዎች የመጀመሪያውን ንባብ አጠቃላይ ታሪክ አንብበው የሚጨርሱበት በደረጃ ከፋፍሎ ያሳያል፡፡ ተማሪዎቹ ታሪኩን አንብበው ከጨረሱ በኃላ መምህራቸው ጋር ያነበቡትንና ተዛማጅነት ያላቸውን ጉዳዮች በማንሳት የሀሳብ ምልልስ ያደርጋሉ፡፡

ይህ ደረጃ ተማሪዎች ፍላጎታቸውን የሚያሰፉበትና ከጓደኞቻቸው ጋር ሀሳብ የሚለዋወጡበት ሲሆን የራሳቸውን የቋንቋ አጠቃቀምና የዓረፍተነገር አወቃቀርንም ለማሳየት ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል፡፡ ለጀማሪ ፀሀፊዎች ዉስብስብ የሆነውን የፅሁፍ ቋንቋ መዋቅር ቀላል ያደርግላቸዋል፡፡ተማሪዎች ጥልቅ ዕዉቀትን እንዲኖራቸውና የመፃፍ ደረጃቸዉንም ከቀላል ወደ በሳል ፅሁፍ ያሳድጋል፡፡

ደረጃ (2) የመፃፍ ብልሀታዊ ባህርይ የሚገለፀው በዚህ ደረጃ ነው፡፡ መር የመፃፍ ትምህርት ለፈጣን ተማሪዎች የመፃፍ ችሎታቸውን ለማሳደግ እድል ይፈጥራል፡፡ የእነዚህ ተማሪዎች የመፃፍ ብልሀታዊ ባህርይ እንደምሳሌ በመዉሰድ ለሌሎች ተማሪዎች መነሳሳትን እንዲፈጥሩ ማድረግ የመምህሩ ድርሻ ነው፡፡

ፍላወርና ሀይስ (1981)ን በመጥቀስ ጊብሰን (2008) እንደአብራሩት በመር መፃፍ ጊዜ የመምህሩ ፍላጎት ተማሪዎች ተነሳሽነት ኖሯቸው ጥሩ አድርገው እንዲፅፉ ፣ጥሩ የሆነ የሀሳብ አጨራረስ እንዲኖራቸው፣ የተስተካከለ የሀሳብ ፍሰትን እንዲከተሉ እንዲሁም ተገቢነት ያለው የስርዓተነጥብ አጠቃቀምና ግልፅነት ያለዉ ማብራሪያ መስጠት እንዲችሉ በመሆኑ መምህሩ ተከታታይነት ያለው እገዛ ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን በፍጥነት እነዚህን ነገሮች እንዲያስተካክሉ የሚጠበቅ ከሆነ በተማሪዎች ስኬታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው፡፡ ምክንያቱም መፃፍ አእምሮአዊ የሆነ ሂደት (Process) አለው፡፡

ደረጃ (3) ይህ ክፍል ደግሞ ተማሪዎች በተናጠል የሚፅፉበትንና መምህሩ ጠንካራ ድጋፍ የሚሰጥበት ነው፡፡ መር መፃፍ ለረጅም ሰዓት የሚፃፍበት ሳይሆን የተማሪዎችን ቀጣይነት ያለዉ ልምምድ የሚጠይቅ ነው፡፡

የመፃፍ ክሂልን ስኬት ላይ ለማድረስ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ ማድረግና ተማሪዎችን የተሟላ ፅሁፍ እንዲያዘጋጁ ማበረታታት ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹ በግላቸው ተከታታይነት ያለው ልምምድ በማድረግ የመፃፍ ደረጃቸውን ለማሳደግ ዉስጣዊ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ይጠይቃል፡፡

ተማሪዎቹ ከዚህ ቀጥሎ ምን ሊፅፉ ይችላሉ? የሚለውን ጥያቄ በዚህ ደረጃ ይመልሳል፡፡ ይኸውም ተማሪዎቹ ከዚህ በፊት ባሳለፏቸው ደረጃዎች ላይ ያገኙትን ግንዛቤ አሳድገው አንጊ በሆኑ ይዘቶች ላይ ራሳቸውን ችለው የሚፅፉበትን ሲሆን ጥሩ የፃፉ የሚበረታቱበትና የፃፉትን ፅሁፍ ተገምግሞ ግብረመልስ የሚሰጥበት ደረጃ ነው፡፡ መምህሩ ተማሪዎቹ ምን እንደሚፅፉና ለምን እንደፃፉ በመጠየቅ የተረዱበትን መጠን ያረጋግጣል፡፡

ጊብሰን (2008) እንደገለፁት ጀማሪ ፀሀፊ የመፃፍ ችሎታውና የመጻፍ ተነሳሽነቱ አድጓል የሚባለዉን የሰዎችን አመለካከትና ትኩረት ሲስብ ፣ የሰዎችን ሀሳብ መቀየር ሲችል ፣ ፀሀፊው ሌሎች የመረጃ ምንጮችን ሲጠቀም፣ ቁርጥራጭ ሀሳቦችን ተቆጣጥሮ ማዋቀር ሲችል፣ ስለቀጣዩ ፅሁፍ ምን መሆን እንዳለበት ሲወስንና የራሱን ፅሁፍ እራሱ ሲያርም ነው፡፡

ደረጃ (4) በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የፃፉትን ከአንባቢ ጋር ያገናኛሉ፡፡ ይህ ደግሞ የመር ማስተማር ብልሀት የመጨረሻ ደረጃ ነው፡፡ ነገር ግን ለአንባቢ ከቀረበ በኃላ የሚሰጡትን አስተያየትና መመሪያ በመቀበል እንደገና ፅሁፉን ይከልሳሉ፡፡ በዚህ ተግባር ዉስጥ የፀሀፊው ዉሳኔ ትልቅ ቦታ አለው፡፡

በዚህ ደረጃ ላይ የመምህሩ ተግባር ተማሪዎች በየዕለቱ የፃፉትን ድምፃቸዉን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ በማድረግ ተማሪዎች እርስበርሳቸው እንዲተቹና ጥያቄ እንዲጠይቁ ማበረታታት ነው፡፡ በመጨረሻም የተማሪዎችን ፅሁፍ በጥንቃቄ በማንበብ ተማሪዎች የሰጧቸውን አስተያየት እንዴት እንደተቀበሉ ይገመግማል፡፡ የእያንዳንዱ ተማሪ የግል ማህደር (Portfolio) እንዲያዘጋጁ ያበረታታል፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎችን ለዉጥና የደረሱበትን መሻሻል ለማወቅ ያግዛል፡፡ ተማሪዎቹ የተሻለ የመጻፍ ደረጃ ላይ እስከሚደርሱ ድረስ የመምህሩ ክትትል መቋረጥ የለበትም የተማሪዎቹ የመፃፍ ክሂል ችሎታ የተሻለ ደረጃ ላይ ደርሷል የሚባለው ደግሞ አንድ ጠንካራ መልዕክት ማስተላለፍ ሲችልና ችግር ፈቺ መሆን ሲችል ነው፡፡

## 2.3 መር መጻፍ የመጻፍ ክሂል ችሎታንና የመጻፍ ተነሳሽነትን በማሳደግ ረገድ ያለው ጠቀሜታ

መር መጻፍ አንዱ የመጻፍ ክህሎት ስትራቴጂ ነው፡፡ ሆልድችና ቹንግ (2003) ስለ መር መጻፍ ሲያብራሩ “መር መጻፍ ወጣት ጸሃፊያን በመጻፍ ክሂል ዉስጥ ያለውን የቃላትና የአረፍተነገር ትስስርና ረቂቅ ጽሁፍን በአእምሮ በመንደፍ የተዋጣለት ጽሁፍ ለመጻፍ ያስችላል፡፡ በእንደዚህ አይነቱ የመር መጻፍ ልምምድ ስትራቴጂ፣ መምህሩ ታዳጊ ተማሪዎች እንዴት ትርጉም ያለው የመጻፍ ክህሎት ችሎታንና መጻፍ ተነሳሽነትን እንደሚያሳድጉ በጥልቀት በማሰብ የራሳቸውን ምርጫ፣ የሌሎች ተማሪዎችን ምላሽና ተጨማሪ ደረጃን እንዲለማመዱ ይጥራል፡፡

ኦክዝኩስ (2007) ን በመጥቀስ ፓርሰንስ (2001፣13) እንደገለጹት መር መጻፍን ለመለማመድና የተማሪዎችን ክህሎት በራስ የመተማመን ብቃት ለመገንባት የሚከተሉት ምቹ ሁኔታዎች መኖር አለባቸው፡፡ (1) የተማሪዎችን የመጻፍ ጥረት ለማሳደግ መምህሩ ወዲያውኑ ግብረመልስ እንዲያገኙ መጣር አለበት፣ (2) ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል የመጨረሻ ግብ ለመድረስ ችግር ፈች ስትራቴጂካዊ ትምህርት ልምምድን ማወቅ አለባቸው፣(3) ተማሪዎች በግል ራስን ችሎ የመጻፍ ክህሎትንና በቡድን ፕሮጀክት የመጻፍ ልምምድን ማቀናጀት ይገባቸዋል፣ (4) ተማሪዎች የመጻፍ መመሪያዎችን በመጠቀም ለምሳሌ በቃላት፣ አረፍተነገርና ጽሁፍ ደረጃ

ለማሳደግ አጋዥ መተግበሪያዎችን መጠቀም አለባቸው፣ (5) በመር መጻፍ ተማሪዎች ጊዜያቸውን በአግባቡ ተጠቅመው መጻፍን መልመድ አለባቸው፡፡

ፕራይሜሪ ናሽናል ስትራቴጂ (2007፣6) እንደገለጸው መር ብልሀት የመጻፍ ችሎታንና የመጻፍ ተነሳሽነትን ለማሳደግ ያሉት ጠቀሜታዎች፡-(1) መምህሩ የመጻፍ ክሂልን በተማሪዎች ፍላጎት ልክ ለማስረጽ ያስችለዋል፣ (2) ለእያንዳንዱ ተማሪ የመማር ተነሳሽነትን ይፈጥራል፤ የመር ጽሁፍ ልምምድ የቡድን ተግባር ቢሆንም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎት በማጤንና ግብረመልስ በመስጠት ይረዳቸዋል፡፡ (3) የተማሪዎችን አቅም በመገምገም ከበድ ወዳለ የቡድን ስራ በማሸጋገር አቅማቸውን ያጎለብታል፡፡ (4) ስለመጻፍ ክሂል ምንነት በማወያየት የተማሪዎችን የተሳትፎ መጠን ያሳድጋል፡፡ (5) ተማሪዎችን በአንድ ሀሳብ ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ በራስ የመተማመን ችሎታቸውን ያዳብረዋል፡፡ (6) መምህሩ ተማሪዎች ያከናወኑትን ወዲያውኑ ግብረመልስ ለመስጠት ከማስቻሉም በላይ ወደፊት መሻሻል ስለሚገባው ተግባር ለመወያየት ያስችላል፡፡

## 2.4 መር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀትን መተግበሪያ ዘዴዎች

ጊብሰን (2012) ስለ መር መጻፍና የመጻፍ ክሂል ችሎታ ሲገልጹ አናሳ ቡድኖችን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል የሚመራ የማስተማሪያ ብልሀት ነው፡፡ የተማሪዎችን የየእለት ተሳትፎና ተግባር በማየትም ቡድኖችን መቀያየር ይቻላል ይህ ደግሞ የመጻፍ ትምህርቱን አሰልች እንዳይሆን ያደርጋል፡፡ በዚህ መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀት ሙሉውን የክፍል ተማሪ በተመሳሳይ መንገድ የመጻፍ ትምህርቱን ማስተማር ይቻላል፡፡ ግልጽና የመጋራት ልምድን እንዲተገብሩ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን የእለት ልምምድ ስትራቴጂ በምሳሌ እንዲረዱትም ያግዛል፡፡ መር መጻፍ የቡድን ተሳትፎ ቢሆንም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎ በማጤን የሚቸግራቸውን ለይቶ በማወቅና ወደ ቡድኑ በማምጣት ግብረ መልስ በመስጠት ችግሮችን ይፈታሉ፡፡ መር መጻፍ በማንኛውም የመጻፍ ሂደት ይከናወናል፡፡ ይህም በጋራ ከመጻፍ ክህሎት /Shared Guided writing/ ክፍል ጋር ተጣምሮ ይሄዳል፡፡ ይህ ተግባር የሚከተሉትን ይይዛል፡፡

## 2.4.1 ጥያቄ በመስጠት

ጥያቄዎች ለመር የመጻፍ ብልሀት ጉልህ ሚና አላቸው፡፡ ጥያቄዎች መረጃን፤ እውነታንና ማስረጃን /facts/ እንድናስታውስ ይረዱናል፡፡ ጥያቄዎች የተማሪዎችን ያለፈ ልምድና ተሞክሯቸውን እንዲያስታውሱም ይረዳቸዋል፡፡

ብራውን (2004፣234) ሲያብራራ መር መጻፍ የጥያቄና መልስ ተግባር ሲሆን ተከታታይ ጥያቄዎችን በመስጠት መጻፍን ማስተማር አፋጣኝና ተገቢ መልስ የመጻፍ ክህሎትን ማሳደግ ነው፡፡ በሌላ በኩል ሆግ (1996፣2) ሲገልጽ ተማሪዎች ለመጻፍ መጀመሪያ ስለሚጽፉት ነገር ሀሳብ ሊመጣላቸው ይገባል፡፡ አንዱ ሀሳብ የማፍለቂያ ዘዴ ማስታወሻ በመያዝ ሀሳብን የማሰባሰብ ክህሎት ነው፡፡

በተጨማሪም ሁፍ (1994፣ 95) እንደገለጸው የጥያቄ አስፈላጊነት ምርመራ፣ መመሪያና ማበረታቻ ሆኖ በማገልገል ይጠቅማል፡፡ የምርመራ፡- መምህሩ ተማሪዎች ርእሱን ስለማወቃቸውና አለማወቃቸውን ስለሚጽፉት ነገር የእውቀት ደረጃቸውን ለማወቅ ያስችለዋል፡፡ የመመሪያ፡- ተማሪዎች በፊት የሚያውቋቸውን ቁሳቁሶች አዲስ ከሚጠቀሙበት ቁሳቁስ ጋር በማቀናጀት እንዲማሩ ያግዛቸዋል፡፡ የማበረታቻ፡- ደግሞ ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት በትኩረት እንዲሳተፉና ሀሳባቸውን በመሰብሰብ የሚያስቡትን ተግባር እንዲተገብሩ ማስቻል ነው፡፡ ተከታታይና በክፍለ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ በመሆን ቀጣይና የማይቋረጥ ትምህርት ሆኖ ልምዱ እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡

## 2.4.2 ስእል በመስጠት፡-

ስእል ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚያነሳሳቸው አንዱ መንገድ ነው፡፡ መምህራን የተማሪዎችን ፍላጎት ባማከለ ሁኔታ የተለያዩ ስእሎችን በመሳል በጽሁፍ እንዲገልጹ ማድረግ ይችላሉ፡፡

ስእሎቹን በፎቶ ግራፍ መልክ የሰዎችን፣ ቦታዎችንና በአካባቢ የሚገኙ ነገሮችን በማካተት ከመጽሄት፣ ጋዜጣና የቀን መቁጠሪያ ላይ ያሉትን በመጠቀም ሊሆን ይችላሉ፡፡ የተለያዩ ስእሎችን በመጠቀም በቋንቋ ትምህርት ክፍል ስለምንነታቸው ስለአጠቃላይ ሁኔታቸው፣ ዓይነታቸው፣ መጠናቸውና ቀለማቸውን እንዲጽፉ ማበረታታት ያስችላል፡፡

ሀርመር (2004፣69) ስለስእል በቋንቋ ትምህርት አስፈላጊነት ሲገልጽ የስእሉን ታሪክ፣ ምን እንደሚመስል፤ ምን ስሜት እንደሚሰጥ፣ ሽታውን፣ ጣእሙን፣ ድምጹን፣ እና ያዩትን ነገር በፍጥነት በመረዳት ዝርዝር ሁኔታውን እንዲጽፉ ግልጽ ትእዛዝ በመስጠት በተማሪዎች ጽሁፍ ውስጥ መካተት የሚገባውን እንዲጽፉ ያስችላል፡፡ ስለአንድ ሰው ስዕላዊ /Descriptive/ ጽሁፍ ተማሪዎች ሲጽፉ፣ሰውየውን መልክና አካባቢው ምን እንደሚመስል ሊጽፉ ይችላሉ፡፡ ስለአንድ ነገር ትዕይንት አጠቃላይ ገጽታ በአንባቢ አእምሮ ስዕላዊ ገጽታውን በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ያስችላል፡፡

## 2.5.የቀደምት ጥናቶች ክለሳ

ሀንዲያኒና ሌሎች (2013) መር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ተነሳሽነትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለማሳየት ቢሞከርም ምን ያህል ከፍ አድርጓል የሚለውን ጥያቄ በግልጽ አልመለሰም፡፡ በተጨማሪም የመጻፍ ክሂልን የሚያደናቅፉ ጉዳዮችን አልገለጹም፡፡ ሉሀ (2014) ግን ለመግለጽ በመሞከራቸው ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡ እንደአብነት የጠቀሷቸውም፤በቂ ያልሆኑ የማስተማሪያ ቁሶች፣የማስተማሪያ ዘዴዎች፣አላስፈላጊ የሆነ የተማሪዎች ጭንቀት ናቸው፡፡

ማካርተር (2002) የPHD በመመረቂያ ጽሁፋቸው ላይ እንደገለጹት 11ኛ ክፍል ያጠናቀቁ 133 ተማሪዎችን በናሙናነት ወስደው ሲያጠኑ የማጠቃለያ ፈተና ዉጤታቸው ዝቅተኛ ነበር፡፡ ለዚህም ምክንያት ነው ብለው በጥናታቸው ያረጋገጡት፣የመጀመሪያው የተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ያለመኖርን ነው፡፡ በተጨማሪም፣ተማሪዎች የመጻፍ ትምህርትን ግብ ለይተው ያለማስቀመጣቸው፣ከጭንቀት ነጻ ሆነው ያለመጻፋቸው፣ግልጽ የሆነ ግብረ መልስ ያለመስጠታቸው የመጻፍ ትምህርት ዉጤታቸውን ዝቅተኛ አድርጎታል፡፡

በናጀሪያ ዉስጥ አህማዱ ቤሎ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋ ትምህርት ክፍል በመለስተኛና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ የተጠና ጥናት እንደሚያመለክተው የተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነታቸው በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ የመጻፍ ተነሳሽነታቸው ዝቅተኛ መሆን የመጻፍ ፈተና ዉጤታቸውን ዝቅ እንዲል አድርጎታል፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የተጠቀሰው ተለምዷዊ የሆነ የማስተማር ሂደትን መከተላቸው ነው፡፡ ይህም ተለምዷዊ የማስተማር ሂደት አእምሮ ጨመቃን በመጠቀም፣ መምህሩ ምንም እገዛ ሳያደርግላቸው ርእስ ይሰጣቸውና በተሰጣቸው ርእስ ስር እንዲጽፉ ይደረጋሉ፡፡ ተማሪዎች ከመምህሩ የሚጠብቁት የሚሰጣቸውን ዉጤት ብቻ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ስህተታቸውን የሚያስተካክሉበት እድል ያጣሉ (አኑዊርቲኒ፣ እና ሌሎች 2012)፡፡

የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች በሚል አጥኚው የጠቀሳቸው፡- በቂ ያልሆኑ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች፣ የማስተማሪያ ዘዴ ችግር፣ በመጻፍ ትምህርት ጊዜ አላስፈላጊ የሆኑ የተማሪዎች ጭንቀት፣ የቋንቋውን ሰዋስው ያለማወቅ ችግርና የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመቀያየር የማስተማር እጥረት መኖር የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት የሁለት ክፍል ተማሪዎች በእጣ ንሞና ተወስደው የቅድመ ፈተና አማካይ ዉጤታቸው 35.2 ነው፡፡ እነዚህን የሁለት ክፍል ተማሪዎች አንዱን ክፍል የቁጥጥር ቡድን ሌላውን ደግሞ የሙከራ ቡድን በማድረግ ለሙከራ ቡድኖች በሳምንት አንድ ቀን ለ30 ደቂቃ ያህል ለተከታታይ አራት ሳምንት መር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀትን ተግባራዊ በማድረግ የመጻፍ ክሂልን ሲለማመዱ ቆይተው ድህረፈተና ተፈተኑ፡፡ ዉጤታቸውም የቁጥጥር ቡድኖቹ 36 ሲሆን በመር ማስተማር ብልሀት የተማሩት ደግሞ 62.1 ነበር፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት ዉጤት መሰረት መር መጻፍን የማስተማር ብልሀት የመጻፍ ችሎታንና ተነሳሽነትን ከማጎልበት አኳያ ዉጤታማ መሆኑን ያሳያል፡፡

በዳምፖሰር ማሀስ ራስ ዋቲ ዩኒቨርሲቲ በሉህ (2014) የተጠና ጥናት እንደሚገልጸው በሥላቲ ትምህርትቤት የሚገኙ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታቸው ከክፍል ደረጃቸው በታች መሆኑ አጥኚዋን እንድታጠና አነሳስቷታል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር የተካሄደው፣ መር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሃት የመጻፍ ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለዉን ሚና ለመፈተሽ ነበር፡፡ ለዚህም የተመረጡት የአንድ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል ዉስጥ የሚማሩት ሀያ ሰባት ተማሪዎች ሲሆኑ 16ቱ ወንዶች 11ዱ ደግሞ ሴት ተማሪዎች ናቸው፡፡

ለጥናቱ የተመረጡት ተማሪዎች በሙሉ ቅድመፈተና ተፈትነው አማካይ ዉጤታቸው 48.4 ነው፡፡ እነዚህ ቅድመፈተና የተፈተኑ ተማሪዎች ለሁለት ተከፍለው ግማሾቹ መር መጻፍን የማስተማር ብልሀትን መሰረት በማድረግ ተከታታይነት ያለው ትምህርት ተሰጣቸው፤ ግማሾቹ ደግሞ የቁጥጥር ቡድን በመሆናቸው ምንም አይነት እገዛ ሳይደረግላቸው ድህረፈተና ተፈተኑ፡፡ ዉጤታቸውም በመር የማስተማር ብልሀት የተማሩት 77.1 አማካይ ዉጤታቸው ሲሆን የቁጥጥር ቡድኖች ደግሞ 53.6 በመሆኑ ልዩነት አሳይቷል፡፡

ሉህ (2014) ማጠቃለያ ስትሰጥ መር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሃት የተማሪዎችን ዉጤት ብቻ ሳይሆን ተነሳሽነታቸውን፣ የመጻፍ ፍላጎታቸውን፣ ተሳትፏቸውን እንዲሁም ደስተኛነታውንም ጭምር እንደሚያሳድግ በጥናቷ አረጋግጣለች፡፡

እነዚህን ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው መር የመጻፍ ክሂልን ማስተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ችሎታንና ተነሳሽነትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና መፈተሻቸው ሲሆን የሚለያዩት ደግሞ በዚህ ጥናት የመጻፍ ችሎታንና የመጻፍ ተነሳሽነትን የሚያደናቅፉ ጉዳዮችን ለመፈተሽ አልተሞከረም፡፡ በተጨማሪም ጥናቶቹ በዉጭ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ችሎታና ተነሳሽነት ላይ የተጠኑ ሲሆኑ ይህ ጥናት ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ችሎታና ተነሳሽነት ላይ የተሰራ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት፡-የአጠናን ዘዴ

## 3.1.የጥናቱ ስልት

ይህ ጥናት የተከናወነው ቅድመፍትነታዊ የምርምር ስልትን መሰረት አድርጎ፣ የአንድ ቡድን ቅድመና ድህረፈተናን ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡ ጥናቱ መጠናዊና አይነታዊ የመረጃ አተናተን ስልትን ተግባራዊ በማድረግ የተገኘውን የማጠቃለያ ዉጤት ያሳያል፡፡

## 3.2.የጥናቱ ተሳታፊዎች

የጥናቱ ተተኳሪዎች በሆጤ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት በ2010 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ በ11ኛ የክፍል ደረጃ እየተማሩ ያሉተማሪዎች ናቸው ፡፡

ትምህርትቤቱ የተመረጠው በአመች የእጣ የንሞና ዘዴ ሲሆን፣ በሌሎች አጎራባች ትምህርትቤቶች ጥናቱ ቢካሄድ አጥኝዋ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎችን በቅርብ ለመከታተል በመደበኛ ስራዋ ላይ ተጽዕኖ ስለሚፈጥርና መረጃ ለመሰብሰብ ምቹ ስለማይሆን ነው፡፡

የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት የ10ኛና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀገር አቀፍ ብሔራዊ ፈተና የሚፈተኑ በመሆናቸው፣ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ፣ ለትምህርትቤቱ አዲስ ከመሆናቸው በተጨማሪ ህፃናት ስለሆኑ በዉጤቱ ላይ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር ተፈላጊውን መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ስላልታመነባቸው ነው፡፡

ስለዚህ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑበት ምክንያት ከሚማሩበት የክፍል ደረጃና ካላቸው ዳራዊ የመፃፍ ክሂል ችሎታቸው አንጻር በመር የመፃፍ ብልሃት ትምህርቱን በመከታተል ብሎም ብልሃቱን በመጠቀም የመጻፍ ሥራቸውን ማከናወን ይችላሉ ተብሎ ስለታሰበ እና ለጥናቱ ትክክለኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ስለታመነባቸው ነው፡፡

በዚህም መሰረት በትምህርትቤቱ በ2010 ዓ.ም በ14ቱ የመማሪያ ክፍሎች በመደልደል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የጥናቱ አካላይ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር በ14ቱ የመማሪያ ክፍሎች የተደለደሉትን ተማሪዎች የሚወክል የመማሪያ ክፍል ለማግኘት፣ እኩል እድል ሰጭ በሆነው በምድብ የእጣ ናሙና ዘዴ (cluster sampling) አንድ የመማሪያ ክፍል እንዲመረጥ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ዕጣው የወጣበት የመማሪያ ክፍል ተማሪዎች ብቻ በተጠኝነት ተመርጧል፡፡

በቅድሚያ የሁሉም ክፍል ተማሪዎች የችሎታ ስብጥር እንደከዚህ በፊቱ የትምህርትቤቱ አሰራር የ2010 ዓ.ም ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ስለሆነ ከትምህርትቤቱ ምክትል ርዕሰ መምህር አጥኚዋ በመጠየቅ የተማሪዎች አደላደል የችሎታ ስብጥርን ታሳቢ ያደረገ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ጥናቱ በሙከራ ላይ የተመሰረተና ሁሉም የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታቸው በአብዛኛው ተመሳሳይ በመሆናቸው የተጠኚ ተማሪዎች ቁጥር በዚህ መወሰኑ የግድ ሆኗል፡፡

## 3.3.የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የምርምሩን አላማ መሰረት በማድረግ ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ለመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሎት ላይ ዉለዋል፡፡

### 3 3.1.ፈተና

በምድብ ዕጣ ናመና (claster sampling) በተሳታፊነት የተመረጡ ተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ የሚለካ ቅድመና ድህረትምህርት ፈተና አንድ አይነት ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡ ፈተናው ሶስት ክፍሎች ሲኖሩት የመጀመሪያው ጅምር ሀሳብን በመጨረስ ድርሰት መጻፍ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የሀሳብ ፍሰትን ጠብቆ ቢጋር (አስተዋጽኦ) መንደፍ ሲሆን ሶስተኛው የነደፉትን ቢጋር (አስተዋጽኦ) መሰረት አድርገው ድርሰት መጻፍ ነው፡፡ ፈተናው የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ፈተናው በአጥኝዋ ተዘጋጅቶ በአማካሪዋና በሌሎች ባለሙያዎች ታይቶና አስተያየት ተሰቶበት ከተስተካከለ በኂላ የዋናው ጥናት ተሳታፊዎች የተመረጡበትን ዘዴ በመጠቀም በተመረጡ በጥናቱ ባልተካተቱ የ11ኛ R10 ተማሪዎች ላይ ሙከራ ጥናት ተካሂዷል፡፡ በጥናቱም የተገኘውን ዉጤት በሶስት አራሚዎች መካከል ያለው የአስተራረም ስምምነት በአራሚ ዘለል አስተማማኝነት (inter rater reliability) ተሰልቶ .975 በመሆኑ ከፍተኛ ስምምነት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ በሙከራ ጥናቱ ላይ ያጋጠመውን የሰአት ማነስ በማስተካከል ወደ 2:30 በማሳደግ በ18/8/2010 ለጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ፈተናው ተሰጥቷል፡፡ ተማሪዎቹም በፈተናው ላይ ስማቸውን ሳይሆን የተሰጣቸውን የኮድ ቁጥር እንዲመዘግቡ ተደርጓል፡፡

ፈተናው በአጥኝዋ ተሰብስቦና የፈተና ወረቀቶች ኮፒ ተደርገው በሁለት ረዳት መምህርና በአጥኝዋ ታርሟል፡፡ ውጤቱን አስተማማኝ ለማድረግ ማረው (1996) በመጻፍ ሂደት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ነጥቦች፡-የአረፍተነገር አወቃቀር፣ በየአንቀጽግንባታ፣ የአንቀጽ አወቃቀር፣ ግጥምጥምነት፣ የአንቀጽ ቀመር መሰረት በማድረግ ሶስቱም አራሚዎች በጽሁፉ ላይ ያላቸው የአስተራረም ስምምነት በአራሚ ዘለል አስተማማኝነት (Inter rater reliability) ተሰልቶ 0.985

በመሆኑ ከፍተኛ ስምምነት መኖሩን ስላመለከተ ተቀባይነቱ ተረጋግጦ የሶስቱ አራሚዎች ተደምሮና ለሶስት ተካፍሎ የተገኘው አማካይ ውጤት ተመዝግቧል፡፡

በመቀጠል በተጠኚነት የተመረጡት የ11ኛ R7 ተማሪዎች መደበኛውን ትምህርት ከሚማሩበት ሰዓት ውጪ በሳምንት ሁለት ቀን በቀን ለ1፡00 ሰአት ለአንድ ወር ያህል በመር የመጻፍ ብልሃት የመፃፍ ክሂል እንዲማሩ ከተደረገ በኋላ ድህረፈተና ተፈትነዋል፡፡ እንዲሁም በመማር ማስተማሩ ሂደትም የተጠኚው ክፍል ተማሪዎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ፣ የእርስበርስ ተራክቦ እና ከመምህሩ ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት ተመዝግቧል፡፡

በጥናቱ የመጣውን ለውጥ ወይም ዉጤት ለማወቅ ከትምህርቱ በኋላ ተሳታፊዎች የመጻፍ ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል፡፡ የመጨረሻው ፈተና አላማ ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ በጉልህ የሚታየውን የመጻፍ ችሎታ መፈተሽ ነው፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች በመር መጻፍን ከተለማመዱ በኋላ በቅድመፈተናው የነበረውን ሂደት በማጠንከር በተመሳሳይ ፈታኞች፣ በተመሳሳይ ክፍልና ሰአት ተፈትነዋል፡፡ የተሳታፊዎቹ ፈተና በቅድመትምህርት መመዘኛ መሰረት፣ የቅድመትምህርት ፈተናው በታረመበት መንገድ በሶስት አራሚዎች ከታረመ በኋላ አማካይ ዉጤቱ ተመዝግቧል፡፡

### 3.3.2.የጽሁፍ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው የካሚንግ፣ ኪምና ኢዋንዛይ (2007) የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መስፈርትን መነሻ ተድርጎ ነው፡፡ በጽሁፍ መጠይቅ መረጃ መሰብሰብ ያስፈለገው በፈተና ከሚፈተሸው ተላውጦ ውጭ ያለውን ለመፈተሸ ሲሆን በፈተና ለሚፈተሸው ተላውጦም ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ ሲዘጋጅ በአጥኝዋ አማካሪና በሌሎች ባለሙያዎች ከተገመገመ በኋላ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በማድረግ ማስተካከያ ተደርጎበት በስራ ላይ ዉሏል፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ የተዘጋጀው በሁለት መንገድ ነው፡፡አንደኛው ዝግ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ይህም 11 ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን በሬቲንግ ስኬል መሰረት የተዘጋጀ ነው፡፡ለእያንዳንዱ ጥያቄዎች አራት አማራጮች ያሉት ሲሆን 1=አልስማማም፣ 2=በጣምአልስማማም፣ 3=እስማማለሁ፣ 4=በጣምእስማማለሁ የሚሉ ናቸው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ክፍት ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ይህም ሁለት ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን ተጠኝዎች፣ መር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀት በመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ያለዉን ሚና በተመለከተ ያላቸውን አመለካከት ለመፈተሽ ያስችላል፡፡

መጠይቁም በዋናው ጥናት ላይ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት የዋናው ጥናት ተሳታፊዎች በተመረጡበት የናሙና አመራረጥ መሰረት በተመረጡ የአንድ ክፍል ተማሪዎች (11ኛR10) ላይ የሙከራ ጥናት ተካሂዷል፡፡ የተገኘውንም መረጃ በአስተማማኝነት መገመቻ ቀመር (ክሮንባ አልፋ) በማስላት የተገኘው ዉጤት 0.819 በመሆኑ አስተማማኝነቱ ተረጋግጦ በዋናው ጥናት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ መጠይቁ ለተሳታፊዎች የተሰጠው ከቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት በኋላ ነው፡፡

## 3.4.የማስተማሪያ ቴክስት አዘገጃጀት

በዚህ ጥናት ለሙከራ ቡድኑ መር የመጻፍ ክሂልን ማስተማሪያነት የሚያገለግል ቴክስት ዝግጅት የፒነካስ (1982)ና ራሚስ (1983) አሻሽለው ያዘጋጁት የመጻፍ ማስተማሪያ ሞዴልን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በሞዴሉ መነሻነት በመር መጻፍ የመጻፍ ክሂልን የሚማሩትን ተማሪዎች የክፍል ደረጃ መሰረት ያደረገ፣ ከተማሪዎች የአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር፣ ከባህል፣ ስነምግባር፣ ማንነትና ማህበራዊ ሁኔታን ከተማሪዎች እይታ አንጻር የሚገልጹበት ነው፡፡ ቴክስቱ አራት ክፍለትምህርቶች አሉት፡፡ አንዱ ክፍለትምህርት በአንድ ወይም በሁለት ክፍለጊዜያት ይጠቃለላል፡፡ ሁሉም አሀዶች መር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀትን ለማስተማር የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

## 3.5.የአጠናን ሂደት

በትምህርትቤቱ አሰራር መሰረት በትምህርት አመቱ መጀመሪያ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በ10ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና፣ በየትምህርት አይነቱ ባስመዘገቡት ዉጤት መሰረት ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ዉጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎችን የትምህርትቤቱ የሥርአተትምህርት ኮሚቴ በየክፍሉ በተመጣጣኝ ቁጥር መድቧል፡፡

የጥናቱን አካባይ ለመምረጥ ትምህርትቤቱን በአመች የእጣ ናሙና ተመርጦ 14ቱን የ11ኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎችን እጣ ዉስጥ በማስገባት ከእድል ሰጭ የናሙና አወሳሰድ የምድብ እጣ ናሙናን በመጠቀም የ11ኛ R7 ክፍል ተመርጧል፡፡ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት ጥናቱ ለሚከናወንበት ለሆጤ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ርእሰ መምህር፣ ለጥናቱ ተግባር የሚያስፈልገውን ማንኛውም ትብብር እንዲደረግልን የሚጠይቀውን የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ደብዳቤ በማቅረብ ለትምህርትቤቱ አስተዳደር ጥናቱ የሚካሄድበትን ክፍልና የተሳታፊዎችን ማንነት በመግለጽ እዉቅና ተሰጥቷል፡፡

ቅድመፈተናው በ18/8/10 ዓ.ም ከ9፡30-12፡00 ሰአት ከተሰጠ በኋላ በአጥኝዋና በሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ታርሞ አማካይ ዉጤቱ ተመዝግቧል፡፡ በመር ማስተማሪያ ብልሀት መለማመድ የተጀመረው በ21/8/2010 ሲሆን በሳምንት ሁለት ቀን (ሰኞና ረቡዕ) ከ9፡30-10፡30 ሰአት መደበኛ ሆኖ ትምህርቱ ተሰቷል፡፡

በልምምዱ መጀመሪያ ቀን የተሳታፊዎችን የመር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀት ምንነትና አተገባበር ዳራዊ እውቀት ለመመርመር መሪ ጥያቄዎችን በማባዛት ለተሳታፊዎች ተሰቷል፡፡ ተሳታፊዎችን አራትና አምስት አባላት ባሉት ቡድን በማደራጀት ጥያቄዎችን ተወያይተዉባቸው እያንዳንዱ ተሳታፊ በቃል እንዲመልሱ ተደርጓል፡፡ የሰጡትን ምላሽ አጥኚዋ በማስታወሻ ከመዘገበች በኋላ ግልጽ ባልሆኑላቸው ጉዳዮች ላይ ምጋቤምላሽ በመስጠት የተሳታፊዎችን የመር ማስተማሪያ ብልሀትና አተገባበር ያላቸውን ግንዛቤ ለማሻሻል ተሞክሯል፡፡

ተሳታፊዎች በመር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀት የፈጠረላቸውን ሁነት በመጠቀም (በስዕል ወይም ታሪክን በመንገር)፣ከራሳቸው ገጠመኝ ተነስተው በጣም ያሳዘኗቸው ወይም ያስደሰቷቸው ጉዳዮችን ከቡድን አባሎቻቸው ጋር በመወያየት እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡ በአጥኝዋና በሌሎች ሁለት ረዳት መምህራን አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ ሁልጊዜ ከትምህርት በፊት ለተማሪዎች ተመልሷል፡፡ ለተሳታፊዎች በሚሰጠው ምጋቤምላሽ ፈጥነው ስህተታቸውን ማስተካከል እንዳለባቸው ግንዛቤያቸውን ለማዳበር ጥረት ተደርጓል፡፡

ተሳታፊዎች በመር ማስተማሪያ ብልሀት መማራቸው ያለውን ጥቅምና ተሳታፊዎች ምን እንደሚጠበቅባቸው ገለጻ፣ ክትትልና እገዛ ተደርጓል፡፡ በልምምድ ወቅትም ተሳታፊዎች ድክመትና ጥንካሬዎቻቸው ላይ እንዲወያዩ ተበራተዋል፡፡ ተሳታፊዎችም እርስበርስ አስተያየት እንዲሰጣጡ ተደርጓል፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች ከ9፡30 ሰአት በኋላ ለአራት ተከታታይ ሳምንታት፣ በሳምንት ለሁለት ቀናት በእያንዳንዱ የትምህርት ቀን ለ1፡00 ሰአት ያህል በተዘጋጀው ቴክስት መር ማስተማሪያ ብልሀትን በመተግበር እንዲለማመዱ ተደርጓል፡፡ የቤት ስራ፣ የክፍል ስራ፣ የተናጠልና የቡድን ስራ የተካሄደ ሲሆን ተሳታፊዎች በአግባቡ መከታተላቸውን ለማረጋገጥ መከታተያ ቅጽ በማስሞላት ክትትል ተደርጓል፡፡

ተሳታፊዎች በእረፍት ቀናቸው (ቅዳሜና እሁድ) የነበራቸውን ገጠመኝ (አሳዛኝ ወይም አስደሳች) ከቤታቸው ጽፈው በመምጣት ሁልጊዜ ከትምህርት ሰአት በፊት ሰኞ ጠዋት ለመምህራቸው ሠጥተዋል፡፡ በአጥኝዋና በረዳት መምህራን አማካኝነት ጽሁፉን በማረምና አስተያየት በመስጠት በትምህርት ሳምንቱ በሁለተኛው ቀን ረቡዕ ወረቀቱ ተመልሷል፡፡

ተሳታፊዎች በክፍል ዉስጥ እንዲወያዩ ከተደረገ በኋላ በመር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀት መጻፍ ሂደት ላይ የየራሳቸውን ግንዛቤ ገልጸዋል፡፡ ምን እንደተማሩና ወደፊት ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸውም ተወያይተው የራሳቸውን ዳራዊ እውቀት ከመር ማስተማሪያ ብልሀት ጋር አቀናጅተው መገንዘብ ችለዋል፡፡ ለአያንዳንዱ ትምህርት እንዲሁም ለእያንዳንዱ ተሳታፊ በጽሁፍም ሆነ በቃል ምጋቤምላሽ ተሰጥቷል፡፡

ተሳታፊዎች በልምምዳቸው ጊዜ ከ4-5 አባላት ባሉት ቡድን ተደራጅተው በመወያየት የጋራ ሀሳቦችን አንስተው በየግላቸው በመጻፍ ከመምህራቸውና ከጓደኞቻቸው የሚሰጣቸው ምጋቤ ምላሽ መሰረት አድርገው ስህተቶቻቸውን በማረም ያለቀለትና አጫጭር ጽሁፎችን ጽፈዋል ፡፡

የመጀመሪያው ልምምድ በሁለት ቀናት ተከናውኗል ፡፡ሰኞ በ21/8/10 ዓ.ም እና ረቡዕ 23/8/10 ዓ.ም በነዚህ ቀናት ተሳታፊዎች ከነበራቸው ዳራዊ አውቀት በመነሳት ግንዛቤ ተፈጥሯል ፡፡ ከዚህም ተነስተው የተለያዩ ተግባራትን አከናዉነዋል፡፡

ሁለተኛው ልምምድ በአራት ቀናት የተከናወነ ሲሆን ሰኞ 28/8/10/ ዓ.ም ፣ረቡዕ 30/8/10 ዓ.ም ፣ሰኞ 5/9/10 ዓ.ም እና ረቡዕ 7/9/10 ዓ.ም ተሳታፊዎች አስተዋጽኦ (ቢ.ጋር) ንድፍ ምንነትና አተገባበር ተወያይተው በቃልና በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ በነደፉት አስተዋጽኦ (ቢ.ጋር) መሰረት ባለአምስት አንቀጽ ድርሰት እንዲያዘጋጁ ታዘው አከናውነዋል፡፡ በመቀጠልም በመምህራንና በአቻዎቻቸው ምጋቤምላሽ ተሰቷቸዋል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ሁሉም ተሳታፊዎች ሶስት ጊዜ ጽሁፎችን አቅርበዋል፡፡

ሶስተኛው ልምምድ በሁለት ቀናት ተከናውኗል፡፡ በመጀመሪያው የትምህርት ቀን 12/9/10/ ዓ.ም አጠቃላይ ምጋቤምላሽ ተሰቷል፡፡በሁለተኛው የትምህርት ቀን 12/9/10 ዓ.ም ደግሞ ድህረፈተና ተፈትነዋል፡፡

## 3.6. የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከጥናቱ አላማ አኳያ ተገቢ መረጃዎች በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ ተሰብስቧል፡፡ በቅድመትምህርት ፈተናና በድህረትምህርት ፈተና የተገኘ መረጃ በስርአት ከተደራጀ በኋላ በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስትና በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል፡፡ በተመሳሳይ ተሳታፊዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ለመመርመር በቅድመትምህርትና በድህረትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ በስርአት ተደራጅቶ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር ተሰልቶ ተተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት፡-የጥናቱ ውጤትና ማብራሪያ

## 4.1 የጥናቱ ውጤት

የጥናቱ አንደኛው ዓላማ መር የማስተማር ብልሀቶች የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ የሚያሳድግ መሆኑን መመርመር ሲሆን ለዚህም ይረዳ ዘንድ ጥናቱ ነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት (one Samples t- test) ተሰልቷል፤ ውጤቱም በሠንጠረዥ 1 ተመልክቷል፡፡

ሰንጠረዥ፡-1 ከቅድመ ትምህርት ፈተና የተገኙ ከፍተኛ፣ ዝቅተኛ፣ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት

| | የተጠኝዎች ብዛት | የተጠኝዎች ዝቅተኛው ውጤት | የተጠኝዎች ከፍተኛው ውጤት | አማካይ ዉጤት | መደበኛ ልይይት | የነፃነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | 46 | 31.33 | 69.33 | 47.80 | 9.437 | 45 | 0.000 |

ከላይ በሰንጠረዥ 1 እንደተመለከተዉ በቅድመፈተናዉ የተገኘዉ የተማሪዎች ዝቅተኛዉ ዉጤት (31.33) ከፍተኛዉ ዉጤት ደግሞ (69.33) ሲሆን አማካኝ ዉጤቱ ደግሞ 47.8 ነዉ ፡ ፡መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 9.43 መሆኑን ያመላክታል፡፡

**ሰንጠረዥ፡-2 ከድህረትምህርት የተገኘ ከፍተኛ፣ዝቅተኛ፣አማካይ ዉጤትና መደበኛ ልይይት**

| | የተጠኝዎች ብዛት | የተጠኝዎች ዝቅተኛ ውጤት | የተጠኝዎች ከፍተኛ ውጤት | አማካይ ዉጤት | መደበኛ ልይይት | የነፃነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድህረ ትምህርት ፈተና | 46 | 48.33 | 83.33 | 63.39 | 9.624 | 45 | .000 |

ከላይ በሰንጠረዥ ሁለት እንደተመለከተዉ በድህረፈተናው የተገኘው የተማሪዎች ዝቅተኛው ዉጤት (48.33) ሲሆን ይህም በቅድመፈተናው ከተገኘው ዝቅተኛ ዉጤት ማለትም (31.33) በ17 ያክል ዉጤት መሻሻሉል አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም በቅድመፈተናው ከተገኘው ከፍተኛ ዉጤት (69.33) የድህረፈተና የተገኘው ዉጤት (83.33) በ14 ያክል ዉጤት እንደተሸሻለ ያሳያል ፡፡ይህም መር መጻፍን የማስተማር ብልሀት የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ማሻሻሉን ማየት ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ.3. የቅድመና ድህረ የመፃፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ልዩነት ትንተና**

| | የተጠኝዎች ብዛት | አማካይ ዉጤት | መደበኛ ልይይት | ቲ-ቴስት | የነፃነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | 46 | 47.80 | 9.44 | -19.677 | 45 | 0.000 |
| ድህረ ፈተና | 46 | 63.39 | 9.62 | | | |

***P<0.05**

በሠንጠረዥ 3 በተገለጸው መረጃ የድህረትምህርት አማካይ ዉጤት (63.39) ከቅድመ ትምህርት አማካይ ውጤት (47.8) ጋር ሲነጻጸር የድህረትምህርት አማካይ ዉጤት የሚበልጥ ይመስላል፡፡ በተጨማሪ የቅድመትምህርት መደበኛ ልይይትና (9.44) የድህረ ትምህርት መደበኛ ልይይት (9.62) ሲነጻጸር የድህረትምህርት መደበኛ ልይይት በልጦ ታይቷል፡፡ ሆኖም ግን የቅድመና ድህረፈተና አማካይ ዉጤት እንዲሁ በማየት ብቻ ልዩነት አለ ወይም የለም ብሎ ለመግለጽ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ ስለዚህ በሁለቱ አማካዮች መካከል ያለው ልዩነት በሰታሰቲክስ መረጋገጥ ስላለበት ጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ዉጤቱም ቲ ( 45 = -19.677/p<0.005/ ) በመሆኑ በቅድመና በድህረትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤት መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት መኖሩን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ዉጤት በመር የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ትምህርትን መማራቸው የመጻፍ ችሎታቸውን ከማጎልበት አኳያ አዎንታዊ ሚና እንዳለው ዉጤቱ ሊያሳይ ቺሏል፡፡

የጥናቱ ሁለተኛ ዓላማ መር የማስተማር ብልሃት የተማሪዎችን የመፃፍ ተነሳሽነት ያሳድጋል ወይ? የሚል ሲሆን ለዚህም ይረዳ ዘንድ ጥናቱ የጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ (Paired samples t-test) ተሰልቷል ውጤቱም በሠንጠረዥ 4 ተመልክቷል፡፡

**ሰንጠረዥ 4፡- ቅድመና ድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ልዩነት ትንተና**

| | የተጠኝዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | ቲ-ቴስት | የነፃነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ተነሳሽነት | 46 | 21.15 | 2.49 | -20.143 | 45 | 0.001 |
| ድህረ ተነሳሽነት | 46 | 29.24 | 3.06 | | | |

በሠንጠረዥ 4 እደተመለከተው ከቅድመትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት መጠይቅ አማካይ ዉጤት (21.15) የድህረትምህርት ተነሳሽነት መጠይቅ አማካይ ዉጤት (29.24) የሚበልጥ ይመስላል፡፡ ሆኖም ግን የቅድመና የድህረ ትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት መጠይቅ አማካይ ዉጤትን እንዲሁ በማየት ብቻ ጉልህ ልዩነት አለ ወይም ጉልህ ልዩነት የለም ብሎ ለመግለጽ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ ስለዚህ በሁለቱ አማካዮች መካከል ያለው ልዩነት በስታትስቲክስ መረጋገጥ ስላለበት ጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ዉጤቱም ጉልህ ቲ (45=-20.143 / p <0.005/) ሆኗል፡፡ ከዚህም በቅድመና በድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ዉጤት መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት መኖሩን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህም በመር የመጻፍ ክሂልን ማስተማሪያ ብልሀቶች የመጻፍ ክሂል ትምህርትን መማር የመጻፍ ተነሳሽነትን ከማጎልበት አኳያ አወንታዊ ሚና እንዳለው ሊያሳይ ችሏል፡፡

የመር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀት የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለመመርመር አጥኝዋ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመችው ፈተና ሲሆን የጥናቱን ግኝት የበለጠ ለማጠንከር ተብሎ በሁለተኛነት ደረጃ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የዋለው የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በመር ማስተማሪያ ብልሀት መጻፍን መማራቸው በመጻፍ ተነሳሽነታቸው ላይ ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ ታስቦ ከቀረቡት የጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎች ውስጥ ሁለቱ በክፍት ጥያቄ ተማሪዎቹ ምላሽ የሚሠጡባቸው ናቸው፡፡ በእነዚህ ጥያቄዎችም የሚከተሉትን መረጃዎች ለማግኘት ተችሏል፡፡

የመጀመሪያው ክፍት የጽሁፍ ጥያቄ፣ “በመር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሃት የመጻፍ ክሂልን መማርህ/ሽ በመጻፍ ተነሳሽነትህ/ሽ ላይ ያለውን አስተዋጽኦ ግለጽ/ጭ?” የሚል ሲሆን ይህንን ጥያቄ በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ፡-

- ለመጻፍ ክሂል ትምህርት ከዚህ በፊት የነበረኝ ፍላጎት ዝቅተኛ ነበር፤ አሁን ግን የመጻፍ ተነሳሽነቴ ጨምሯል።
- የመጻፍ ትምህርትን ከባድ አድርጌ ስለማስብ መጻፍ አልወድም ነበር፤ አሁን ይህ አመለካከት ተለውጦ የሚሰጡኝን የመጻፍ ተግባራት በፍጥነትና በፍላጎት አከናውናለሁ።
- ከበፊቱ በተሻለ ተነሳሽነት ኖሮኝ፣ በአካባቢዬ የማየውን ነገር ሁሉ የመጻፍ ፍላጎቴን አሳድጎታል የሚሉ ናቸው።

ሁለተኛው ክፍት የጽሁፍ ጥያቄ፣ "የመጻፍ ተነሳሽነት መኖር የመጻፍ ችሎታህን/ሽን አሳድጎታል ብለህ/ሽ ታስባለህ/ሽ?" የሚል ሲሆን የተማሪዎች ምላሽ ደግሞ 19(41.3%) የሚሆኑ ተማሪዎች አዎ በጣም አሳድጎታል ሲሉ፣ 23(50%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ በፊት ከነበረኝ የመጻፍ ችሎታ ይልቅ አሁን በመጠኑም ቢሆን ተሸሽሏል የሚሉ ናቸዉ። በሌላ በኩል 4(8.69%) ተማሪዎች በፊት ከነበረኝ ችሎታዬ ምንም የተሻሻለ የመጻፍ ክሂል ችሎታ የለኝም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

ተነሳሽነት የመማር ትጋትን ለማምጣት (ለመጨመር) ከሚረዱ ዘዴዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ነው። ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልንም ሆነ ሌሎችን ክሂሎችንና የትምህርት አይነቶችን ለመማር ውስጣዊ ፍላጎትና ተነሳሽነት ወሳኝ ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ትምህርታቸውን በንቃት መከታተል ስለሚችሉ የትምህርት አቀባበላቸው የተፋጠነ እንደሚሆን ይገመታል።

ከዚህ አንጻር የተማሪዎች ምላሽ እንደሚያሳየው፣ በመር የማስተማር ብልሀት የመጻፍ ክሂል ትምህርትን ከተማሩ በኃላ፣ ተማሪዎቹ የተለያየ የመፃፍ ክሂል ክንዋኔዎችን በፍላጎትና በራሳቸው ተነሳሽነት የመስራት አቅም እንዳጎለበቱና የመጻፍ ችሎታቸውም ቀደም ሲል ከነበረው አሁን በተሻለ ሁኔታ እንዳደገ ነው።

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ የቀረቡትን ሁለት ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ ከተማሪዎች የተገኙት ምላሾች የሚያመላክቱት በመር የመጻፍ ክሂልን ማስተማሪያ ብልሀትና በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ መካከል አወንታዊ ተዛምዶ እንዳለ ነው። ለተዛምዶውም ጉልህ ድርሻ ያበረከተው የተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ከፍተኛውን ቦታ መያዙን ነው።

## 4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የጥናቱ የመጀመሪያ አላማ መር የማስተማር ብልሀት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ማሳደጉን መፈተሽ ነበር። ለዚህም ቅድመትምህርት ፈተናና ድህረትምህርት ፈተና አገልግሎት

ላይ ውሏል። በመሆኑም የድህረትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በልጦ ተገኝቷል። ይህም በመር ማስተማሪያ ብልሀትና በመጻፍ ትምህርት መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት መኖሩን አመልክቷል። ስለዚህ በመር ማስተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ትምህርትን መማር የመጻፍ ችሎታን ያዳብራል የሚል መደምደሚያ ላይ ሊያደርስ ይችላል። ምክንያቱም በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች በመር የማስተማሪያ ብልሀት መጻፍን በመማራቸው የመጻፍ ፈተና ውጤታቸው ተሻሽሏል። በዚህ መሰረት በመር ማስተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ትምህርትን መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ የጎላ አስተዋጽኦ እንዳለው ያሳየው ይህ የጥናት ውጤት በጥናታቸው መጻፍን በመር ማስተማሪያ ብልሀት ማስተማር የመጻፍ ትምህርትን ውጤታማ ሊያደርግ እንደሚችል ያመላከቱት ጆሴፍ (2013)፣ ሀንዲያኒና ሌሎች (2013፣) እንዲሁም መር የማስተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ዋነኛ የማስተማሪያ ዘዴ እንደሆነ ያመላከቱት በአህማዱ ቤሎ ዩኒቨርሲቲ (2013) በቋንቋ ትምህርት ክፍል የተጠና ጥናት፣ እንዲሁም ሉህ (2014)፣ ማካርተር (2002) ጥናቶች ጋር የተጣጣመ ሆኖ ተገኝቷል።

መር የማስተማር ብልሀት የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ማሳደጉን መመርመር የዚህ ጥናት ሁለተኛ አላማ ነበር ለዚህም የቅድመና ድህረ የጽሁፍ መጠይቅ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ውሏል። በዚህም መሰረት በቅድመና ድህረትምህርት ተነሳሽነት መጠይቅ አማካይ ውጤት መካከል በስታስቲክስ ጉልህ ልዩነት ታይቷል። ይህም በመር ማስተማሪያ ብልሀትና በመጻፍ ተነሳሽነት መካከል አዎንታዊ ተጽእኖ እንዳለ አመልክቷል። ስለዚህ ተማሪዎች በመር ማስተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ትምህርትን በመማራቸው የመጻፍ ተነሳሽነታቸው ተሻሽሏል የሚል መደምደሚያ ላይ ሊደረስ ችሏል። መር የማስተማሪያ ብልሀት ከተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው የሚል የጥናት ውጤት የሚያመላክተው ሉህ (2014)ና ጆሴፍ (2003) ከተመዘገው ውጤት ጋር ይቀራረባል።

በክፍት የጽሁፍ መጠይቅ የቀረቡት ሶስት ጥያቄዎችም ተማሪዎች ተነሳሽነትን ከመር ማስተማሪያ ብልሀት ጋር አያይዘው በመር ማስተማሪያ ብልሀት መማራቸው የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን ከፍ እንዳደረገላቸውና የመጻፍ ተነሳሽነት መኖር ደግሞ የመጻፍ ክሂል ችሎታን እንደሚያሳድግ ገልጸዋል። ይህም ከሉህ (2014) የጥናት ውጤት ጋር ይመሳሰላል።

# ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያ መደምደሚያና አስተያየት

## 5.1. ማጠቃለያ

መር የመጻፍ ክሂልን ማስተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ችሎታንና ተነሳሽነት ከማጎልበት አኳያ ያለውን ሚና ለመለካት በዚህ ጥናት ሊመለሡ የታሰቡ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡ (1) መር የማስተማር ብልሀት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ያሳድጋልን? (2) መር የማስተማር ብልሀት የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ያሳድጋል ወይ? የጥናቱ አካባቢ በደሴ ከተማ በሆጤ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቤት ነው፡፡ ትምህርትቤቱ በእጣ ንሞና ተመርጧል፡፡ በዚህ ትምህርትቤት 2010 ዓ.ም ካሉት 14 የ11ኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎች መካከል በእድል ሰጭ ናሙና አወሳሰድ ዘዴ የ11ኛ R 7 ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡ በክፍሉ የሚማሩት 46 ተማሪዎች ናቸው፡፡

የአጠናን ዘዴው ቅድመፍትነታዊ (የአንድ ቡድን ቅድመና ድህረፈተና) ሲሆን ለጥናቱ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ለመረጃ መሠብሰቢያነት አገልግሎት ላይ ዉሏል፡፡

ቅድመና ድህረፈተናው እንዲሁም የጽሁፍ መጠይቆች በጥናቱ አማካሪና በሌሎች ባለሙያዎች ማስተካከያ ተደርጎባቸው፣ በሙከራ ጥናት ተፈትሸው አስተማማኝ በመሆናቸው ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች የፒንካስ (1982)ና ራሚስ (1983) አሻሽለው ባዘጋጁት ሞዴል መነሻነት መር ማስተማሪያ ብልሀትን በመጻፍ ክሂል ላይ ለመለማመድ የሚያስችል፣ የተሳታፊዎችን የትምህርት ደረጃ መሰረት ያደረገ፣ ከተማሪዎች የአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ለማስተማር እንዲመች በጥቂቱ መሻሻል ተደርጎ በተዘጋጀ የመር መጻፍን ማስተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ትምህርትን ማስተማሪያ ቴክስቱን መሰረት በማድረግ ለአራት ሳምንት ተለማምደዋል፡፡ በዚያም በቅድመትምህርት ፈተናዉ የነበረዉን ሂደት በጠበቀ መንገድ ተመሳሳይ ፈታኞችና በተመሳሳይ ሰዓት እንዲሁም በተመሳሳይ ክፍል ከቅድመፈተናው ጋር ተመሳሳይ ፈተና በድህረትምህርት ፈተናዉ መረጃ ተሰብስቧል፡፡

ሁለተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ አገልግሎቱም የጥናቱ ተሳታፊዎች በመር ማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ትምህርትን በመማራቸው በመጻፍ

ተነሳሽነታቸው ላይ ያለውን ተጽእኖ ለመመርመር ነው፡፡ ለዚህም የካሚንግ፣ ኪምና ኢዋንዛይ (2007) ያዘጋጁት የጽሁፍ መጠይቅ በአማርኛ ተተርጉሞና ለጥናቱ በሚመች መልኩ ተሻሽሎ በጥናቱ አማካሪና በባለሙያዎች ማስተካከያ ተሰጥቶበታል፡፡ ከዚያም በዋናው ጥናት ላይ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በሙከራ ጥናት (ፓይለት ስተዲ) አስተማማኝነቱ ተረጋግጦ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ መጠይቁ በጥናቱ ተሳታፊዎች የተሞላው ከቅድመትምህርት በፊትና ከድህረ ትምህርት በኋላ ነው፡፡ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታቲስቲክስ ተተንትኗል፡፡

በቅድመትምህርት ፈተናና በድህረትምህርት ፈተና የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን ጥንድ ናሙና ቲ- ቴስትና ነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ በዚህ መሰረት የድህረትምህርት አማካይ ውጤት ከቅድመትምህርት አማካይ ውጤት በልጦ ተገኝቷል፡፡ በአማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ($P<0.005$) ልይይት መኖሩንም በስታትስቲክስ የተገኘ ውጤት አመልክቷል፡፡ ከተገኘው ውጤት በመነሳት በመር ማስተማሪያ ብልሀት መጻፍን መማር የመጻፍ ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና የጎላ ነው፡፡

በቅድመና ድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነትን ለመለካት የጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡ በዚህም መሰረት በቅድመና ድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት መካከል በስታቲስቲክስ ጉልህ ($P=<0.005$) ልይይት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ በመር ማስተማሪያ ብልሀት የመጻፍ ትምህርትን መማር የመጻፍ ተነሳሽነትን ከማጎልበት አኳያ አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዳለው አመልክቷል፡፡

